
# የጌታቸው ሚስቶች



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከጳውሎስ ኞኞ

# የጌታቸው ሚስቶች

ከጳውሎስ ኞኞ

## ማውጫ

ምዕራፍ ፩።9

ምዕራፍ ፪።21

ምዕራፍ ፫32

ምዕራፍ ፬43

ምዕራፍ ፭48

ምዕራፍ ፮።57

ምዕራፍ ፯።67

ስለደራሲው በጥቂቱ74

ይቺን መጽሐፍ ለዘመኔ ላሉ ኢትዮጵያውያን ዘፋኞችና ሙዚቀኞች መታሰቢያ አድርጌአታለሁ።

ከታተመችበት ወር አንሥቶ ላንድ ዓመት የመጽሐፌ መብት የግሌ ነው፤ ከአንድ ዓመት በኋላ መብቱ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ይሁን፤ ከወሰንኩት ጊዜ በኋላ አሳትሞ ለመሸጥ የፈለገ ሁሉ ከድርሰቴ ሳይቀንስም ሆነ ሳይጨምር ሊያራባው ይችላል።

ስሜን ሳይሰርዝ «አሳታሚን እገሌ» ብሎ ማንም ኢትዮጵያዊ ከፈለገ እንዲያራባት የደራሲነት መብቴን ለቅቄአለሁ፤ አሳታሚው የግሉን የመግቢያ ሐተታ በስሙ ቢጽፍ እኔም ሆንኩ ወራሼ አንቃወምም።

# የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

## ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች

እንዴት ናችሁ? ደህና መሆናችን መልካም ነው። «ከሴቶቹ አምባ» መጽሐፌ ቀጥዬ «የአራዳው ታደሰን» አቅርቤላችኋለሁ፤ አሁን ደግሞ ይህን «የጌታቸው ሚስቶች» ያልኩትን አቀረብኩላችሁ።

ይህችኛዋንም መጽሐፌን እንደ አራዳው ታደሰ መጽሐፌ የማውቀውንና የሰማሁትን ታሪክ እያራባሁና እያበዛሁ ጻፍኩት፤ ከማራባቴ በስተቀር ሁሉም የተደረገ እውነተኛ ነገር ነው።

ሥራዬ ለጋዜጣ ወሬ ማቅረብ በመሆኑ «ተበደልን» እያሉ ወሬ የሰጡኝን ሴቶች ታሪክ አጠራቅሜ ለወጉ ታደሰን ቀንደኛ በማድረግ በአራዳው ታደሰ መጽሐፌ ገለጥሁ፤ በየችሎቱ እየተካሰሱ የሰማሁትንና አንዳንድ ወንዶችም ሚስቶቻቸውን ያደረጉባቸውን ወሬ የሰጡኝን አከማችቼ በዚህኛው መጽሐፌ ገለጥኩት።

ባለ ጉዳዮቹ ያወሩልኝ በጋዜጣ እንዲገለጥላቸው ነበር፤ ያገራችን ጋዜጦች ግን ለእንዲህ ዓይነቱ ነገር እምብዛም ዓምድ እንዲሰጠው ስለማይፈቀድና ደግሞ የግል የንግድ ጋዜጣ ስለሌለ በዚያ የማይሆን በመሆኑ ይመከራል ያጫውታልም በሚል ዓላማዬ በዚች ቅፅ አሳተምኩት።

አድርጌቱ ብቻ እርግጠኛ ይሁን እንጂ ስላጻጻፉ እንዳሻኝ በመሰለኝ መንገድ መርቼዋለሁ። በተለይም እውነተኛ ታሪክ የሚገኘው በያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት ዘንጋ ዘንጎች (-//-) ካሉበት ግርጌ ነው፤ በዚያውም ቢሆን ታሪኩን ሳልጥል አጻጻፌን በሚስማማኝ አስኪጄዋለሁ የባለታሪከኞቹ ስም ግን የኔው ፈጠራ ነው።

ታሪኩን ራሱ እንዲያወራ ያስደረኩት ጌታቸውም ቢሆን በመጽሐፌ ውስጥ የሴት ኮከብ እንዲሆን መላውን ታሪክ ደፈደፍኩብት እንጂ ይህ ሁሉ እይሚስት ፍዳ በአንዱ ሰው በሱ ላይ ብቻ የደረሰበት አይደለም።

መጽሐፌ እያንዳንዱን ታሪክ በሚገባ አትተነትንም፤ መንተንተን ቢያስፈልገኝስ ኖሮ ያንዲቱ ዓይናማ ታሪክ በሞላው ነበር፤ ያ እንዳይሆን

ቀንድና ጭራውን ብቻ አስፍሬዋለሁ፤ እኔን ይከፋኝና በዚህ የሚከፋችሁ አይመስለኝም።

በመጽሐፌ ውስጥ ካሉት ስሞች መሐል ጥቂቶች ብቻ የኔው ፈጠራ ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ከነግብራቸው እርግጠኞች ናቸው፤ ከነዚህም ስሞች መሐል ግማሾቹ የቅርብ እውቂያ ያለን ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ባንድ ቀን መተያየትም ብቻ ሥራቸው ለመጽሐፌ የሚስማማ እየሆነ ስላገኘሁት አገባሁት፤ ለምሳሌ ከሲስተር ብስኩት ጋር ምንም እውቂያ የለንም፤ አንድ ቀን ስሟ ሲጠራ በመስማቴ ብቻ ለመጽሐፌ ተጠቀምኩባት፤ ይህን በመሰለው አጻጻፌ ስማችን ተጠራ ባዮች ባይቀየሙኝ እወዳለሁ።

ብዙዎቹ ወዳጆቼ ፍላጎታቸውን ሲያወሩ እሰማ ነበርና ያን የሚገልጉትን ልሰጣቸው የማልችል ምስኪን ፍቱር ሆኜ ሳለሁ በመጽሐፌ ውስጥ ግን ፍላጎታቸውን ሰጠኋቸው። በዚህም በኩል አንድ ምሳሌ ከውጽቱ ላውጣ፤ አዳነች ልጅ ለመውለድ ያላትን ጉጉት ስለማውቅ በመጽሐፌ ውስጥ ሴት ልጅ ወልዳ እልል ተብሎላት አርጋ የማታውቀውን በአራስ ወግ ገንፎ እንድትበላ አድርጌአታለሁ። ይህ ሁሉ አያስወቅሰኝም ባይ ነኝ፤ በዚህ የተነሳም በመጽሐፌ ውስጥ የተጠሩት ሁሉ ባያኮርፉኝ ደስ ይለኛል።

በመጽሐፌ በጉልምስና ወራታቸው አጥር ዘለው ላደጉ ላሁኖቹ አዛውንቶች ደስ አታሰኛቸው ይሆናል፤ ይህም ያለማስደሰቷ አያስከፋኝም፤ የጉልምስናና የእርጅና ወራት ለየቅል ነው፤ አጻጻፌ የሚያስከፋቸው ባለገብስማ ጠጉሮቹ ዕድሜያቸውን ያርዝመውና ባይረግሙኝ እወዳለሁ።

መቼም የሚያጣላን ብልግና የሚባለው ነገር ነው፤ በውነቱ አያጣላንም፤ ኢትዮጵያውያን አንባቢዎች

እንደሌላው ዓለም አንባቢዎች ሁሉ የሚፈልጉትን ንባብ ማግኘት ስላለባቸው ሌላዎቹ ያን መሳዩን ሲጽፉ እኔው ደግሞ ይህን መሳዩን ጻፍኩ።

አንዳንድ ሽበቶዎች «ምክር ለምን አትጽፍም? » ብለውኛል፤ አሁንም እንደገና ዕድሜያቸውን ያርዝመውና ስመልስላቸው መምከር እንደ ዕድሜ ነው እላቸዋለሁ፤ እሳት በሆነው በጉርማሳነት ወራቴ የኔው አመካከር «ያዛት ተከተላት ከበባት ጥለፋት፤

ያቺን ሞንዳላ ልጅ ውሰዳት እቀፋት» ነበር፤ እኔው ግና በይሉኝታም በመሽኮርመም «ነበር» ብዬ ተውኩት፤ ምክርም በወግና በፈሊጥ እንጂ በመነዝነዝ አይደለም ብዬ የማምን የስምንተኛው ሽህ ጐረምሳ ነኝ፤ በትዳር መሐል ወይም ልበለው በመጋባት መሐል ላለው ዝባዝንኬ ነበር «የአራዳው ታደሰ» መጽሐፌ የማይመከረው ወንዶችን ነው፤ ለወንዶቹ ፈንታ ደግሞ ይህቺን መጽሐፍ ከዚያኛው ካስቀደምኩት አስከተልኳት፤ በደረቁ ለመምከር መጽሐፍ ቅዱስ ይበቃናል፤ የኔዎቹ ግን የኔው የጳውሎስ ኞኞ አጻጻፍ እንጂ የሚቱ ጳውሎስ መልእክቶች አይደሉም።

በ «በአራዳው ታደሰ» መጽሐፌ ባለጌ ነህ ያሉኝ አሉ፤ ፍረዱኝ እናንተ የተማራችሁ የስምንተኛው ሺህ ወጣቶች!! ምንኝው ላይ ባለግሁ? መሳሳም በፊደል ነውር ነውን?

በድርሰት ሥራዬ አንድም ባለ ውለታ የለብኝም እርግጥ እኔና መጽሐፌ ውለታ ያደረብን ያቶ ለማ ፈይሳ ነው፤ አቶ ለማ የነ አፍንጮ ተርጓሚ መልካም ደራሲ ናቸው፤ በዚች መጽሐፌ መታተም ዘመን ደግሞ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሥራ መሪ (ዲሬክተር) ስለ ነበሩ በመታተምዋ በኩል ያደረጉልኝ ወሮታ ውለታ ነው።

ጐረምሳ በመሆኔም እንደሁ እንጃ እንጂ ዘፈን እውዳለሁ ለብስጭት ራስ ምታቴ መልካም አስፕሮ ሆኖ ያገኘሁት ዘፈንን ነው፤ አጻጻፌም የሚመራው ወይም የሚካሔደው በዘፈን ነበር። የመንፈሴ ሥራ መሪ የሆኑት ያገሬ ዘፋኞች እየዘፈኑልኝ ይቺን ድርሰቴን ስላከናወንሁ ዘፋኞች ባለውለታዎቾ ናቸው። በኔ ዕድሜ የተጀመረው የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ደስ እያለ ጊዜ አለጊዜ ሁሉ ለሥራዬ መተካዣ እያልኩ ሳዘፍናቸውና ውሀ የማይጠጣ በኤሌክትሪክ የሚንቀሳቀስ ጉሮሮአቸውን ስላደረቅሁት ይቺን መጽሐፌን በዘመኔ ለነበሩ ኢትዮጵያውያን ተጫዋቾች መታሰቢያ ያደረኳት።

ስለዚህ ነው። መታሰቢያነቱ ለባለ ክራሩም ሆነ ለባለ ጊታራው፤ ለባለ ማሲንቆውም ሆነ ለባለ ቫይለኑ ልዩነት የለውም።

እንግዲህ የምልክላችሁ ደብዳቤ እዚህ ላይ አለቀች፤ አሁን እንግዲህ ጌታቸው ታሪኩን እንዲያወራላችሁ አድርጌ ማስጀመሬ ነው፤ ብትወዱልኝ «እሰየው» እላለሁ ብትጠሉብኝ መቼስ ምን አደርጋለሁ «አፍራለሁ»።

በደህና እንሰንብት።

# ምዕራፍ ፩።

እርግጥ ነው ቆንጆ ነች፤ ሳያት ደስ አለችኝ፤ በዳሌዋ ማረከችኝ፡፤ በሽንጥዋ ጣለችኝ፤ በጡትዋ በሽተኛ አደረገችኝ፤ ብታየኝ ገደለችኝ፤ ብትስቅ ቀበረችኝ፤ ድምፅዋን ብሰማ ትንሣኤ ዘሙታን ሆነና አይኔን ገለጥሁ።

አንድ ቀለታ ካቶ ኃይሉ ጋራ እናትዋ ቤት ሔድን፤ ማርታ ቁጭ ብላ ምሥር ትለቅም ነበር፤ ቡናው እንደከተመ አቶ ኃይሉ ለማርታ እናት ለእመት ሙሉነሽ ጉዳይ አለኝ ብለው ይዘዋቸው ወጡ፤ በዚያ ቤት እኔና ማርታ ብቻ ቀረን፤ «ወደድኩሽ» አልኳት «ከምኔው» አለችኝ፤ «ካሁኑ» ብላት «ቸኮልክ» ብትለኝ እፍር አልኩ።

እናትዋ እመት ሙሉነሽ ጠላ ሻጭ ናቸው፤ አባትዋ አቶ አውግቼው ግን በምን አነሳሽኝ አይበሉኝና የሐጂ አብደላን ሸእቅጥ መኪና ላይ ሲጭኑ ቦንዳ ወድቆባቸው ሞተዋል አሉ።

ማርታ ለወጉ ተማሪ ቤት ገብታለች፤ ዕድሜዋ ግን ፲፱ ዓመት ነው፤ ያለችው ደግሞ ገና ፬ኛ ክፍል ነው።

የማርታ አለባበስ እንደ ነገሩ ነው፤ ያሏት ሦስት ቀሚሶች ናቸው። እነሱም ቢሆኑ ሉቲዎች ናቸው፤ ከሦስቱ ቀሚሶች አንደኛው ከቤት የምትለብሰው የሥራ ልብስዋ ነው። ዝንጉርጉሩን ቀሚስ ደግሞ አቶ ኃይሉ በአራት ብር እንደገዙላት ነግረውኛል።

ማርታ የሰው ሥራ ድሀ ብትሆንም በእግዚአብሔር ሥራ ግን የበለጸገች ቆንጆ ነች፤ ማርታን በልብስ የሚበረግጉ የአዲሳባ ጉረምሶች እየናቋት ቆይታለች፤ ማርታም ብትሆን እንደሌሎቹ መሆኑ እያማራት የጨዋ ልጅነቷ ለጉሟት ኖርዋል።

ማርታን ወድደድኳትና ላገባት ወሰንኩ፤ ልብስዋን ሁሉ አለባብሼ አሳመርኳት፤ አንድ ቀን ወደ ኮተቤ ይዣት ሔድሁ ካቶ ማሞ ቤት ጓሮ ከጫካው ውስጥ ሆነን «ማርታዬ? አታገቢኝም? » ብላት «አንተሳ? » አለችኝ

«አገባሻለሁ»

«አገባሃለሁ»

«የኔ ነሻ»

«አንተሳ? »

«ያንቺ»

«እኔም ያንተ»

ከማርታ ጋር ለመጋባት ጨረስን፤ ቤተ ሰቦቼም ጓደኞቼም አወቁልን፤ ከጓደኞቼም መሐል እነ አበበ፤ እነ ደበበ እነ በለጠ ሁሉ አንዳንድ ነገር እየነገሩኝ ሸክ ገባኝ፤ ሐሙስ ለታ ከዘውዴ ጋራ ቼንትሮ ቡና ቤት ተገናኘንና «ይቺን ልጅ ልታገባት ቆርጠሃል? » ቢለኝ «አዎ አልኩት፤ «ይሁና» ብሎ ዝም አለኝ።

«ምነው ምን ሰማህ? » ብለው «ሚስት አትሆንህም አጉል አትክሰር፤ በገዛህላት አልጋና ቁም ሣጥን መኝታ ክፍሏን አጋጊጣ የማንንም ጎረምሳ ታማርጣለች» አለኝ «እንዴት? » ብለው «አይ እኔ ብቻ ያየሁትን ነገርኩህ» አለኝ።

ተበጠበጥሁ፤ በማርታ ላይ የነበረኝ ፍቅር ቀነስ አለ፤ ይነደኝም ጀመር፤ አንድ ቀን ከቤት አመጣኋትና «ሌላ ወደሻል አሉ» ብላት «እኔ? » አለችኝ።

«አዎ»

«የነገው ሚካኤል ገላዬን ይገልብጠው»

«በውሸትም ትምያለሽ አሉ»

«ኸረ እንዲያውም የቁልቢው ገብርኤል ይሰነጣጥቀኝ»

«አልቀየምሽምና ተሳስተምሽ እንደሁ ንገሪኝ»

«ስማ ጌታቸው፤ ሰበብ እንደሁ የምትፈልገው ተወኝ፤ እኔ ግን ባልሠራሁት ሥራ፤ ብቻ እግዚአብሔር ይፍረደው» ብላ ማልቀስ ጀመረች፤

በሴት ልጆች የሚጨክን አንጀት የለኝምና ሌላውን ትቼ አባበልኳት፤ ይቅርታ ጠይቄአት ላባብላት ተኛን።

ሰሞኑን በኔና በማርታ መሐል እየገቡ ብዙ ወሬ ያወሩኛል ብዙ ናቸው፤ እማሆይ ጌጤ እንኳን ቆባቸውን ረስተው «ተው ልጄ ተው» ሲሉኝ ከረሙ፤ እኔ ግን ሟቹ ጳውሎስ በድንገት ያገኘው ክርስቶስ በነገረ ቃል እንዳመነው ማርታን በምትነገረኝ ቃሏ አመንኳት፤ እነ አበበ ግን የውስኪ ማወራረጃ አርገውን ነበር።

ቅዳሜ ወደ አበበ ቤት ሔድሁና ገረዱ ያቀረበችለትን ምሳ ሲበላ ደረስኩበት፤ እንደደረስኩ «አንተ ቀጣፊ? ይህን ሐሰት ነገር መቀባጠሩን ምነው ብትተው? » አልኩት፤ አበበም እንዳቀረቀረ አንድ ጉርሻ ጕርሶ እያላመጠ ቀና ብሎ አየኝና «ትበላ እንደሁ ተቀመጥ» አለኝ፤ «አፈር ብላና ከእንዳንተ ዓይነቱ ወለወልዳ ጋር ምን ይበላል? » አልኩት እሱም አፉን ጭኑ ላይ በነበረው ፎጣ እየጠራረገ «እውነተኞቹ እኔ ወይስ ማርታ? » ቢለኝ ዓይኔን አፍጥቼ በኃይል «ማርታ» አልኩት።

«ማርታ ጨዋ ነች ነው የምትለው? » ቢለኝ

«በቄንጥ ነዋ አልኩት

«እርግጥ በገንዘብ ቄንጠኛ ከመሆንዋ በፊት ጨዋ ነበረች»

«አሁንሳ»

«ባልጋለች»

«በሞቴ አበበ፤ እባክህ ያሆነና ያላየኸውን አታውራ»

«ዓይቻለሁ፤ ሆኗልም»

«ቆይ እሺ ከኔና ካንተ ለማርታ ማን ይቀርባል? »

«አንተ»

«ታዲያስ? »

«ከብት ነሃ»

«እንዴት»

«ሰው ብትሆንማ እኔ ያየሁትን ታይ ነበራ»

«አበበ በጠበጥከኝ»

«ስማ ጌታቸው፤ እኔኮ ስለምወድህ ነው እንጂ ብትፈልግ አሁን አግባት ያ የግል ምርጫህ ነው»

«አበበ አልቀየምህም ብቻ የምልህ»

«የምትለኝ»

«ምን ማስረጃ ታቀርብልኛለህ? »

«ጥሩ ብለሃል ጌታቸው፤ ማርታ እኔን አታውቀኝም፤ አይደለም? »

«ነው»

«ደብዳቤ ልጻፍላትና የምትሰጠኝን መልስ ላሳይህ? »

«ጥሩ፤ በጣም ጥሩ»

«ለመሆኑ ያን ሮዙን ሹራብ ከየት አመጣሁት አለችህ? » «በሰጠኋት ፖኬት መኒ ገዛችው፤ ይሔ ደሞ እርግጥ ነው»

«ቡሽ ጫማውስ? »

«እሱም እንደ ሹራቡ ነው»

«ብራስሌቷስ? »

«ኦ አበበ በሱ አትመን፤ እኔ እራሴ ባለሁበት ምን እኔ ብቻ ለማም አለዩ - አክስቷ ወይዘሮ አጠደ ግብዣ የጠሩን ለታ እጃቸው ላይ አርገውት ማራታ አይታ አማረኝ ብትላቸው በኔው ፊት ነው ፈተሽ ውሰጂ ያሏት።»

«ዱሮ የሺሊንግ ሻሽ ያልቸሯት አሁን ምን ዓይተው የወርቅ ብራስሌት ሰጧት? »

«ኖ ይሔን አትበል አበበ - አየህ ሲያገኙ መውደድ ሲያጡ መጥላት የሰው ባሕሪ ነው፤ ስለዚህ»

«አሁን ጌታ ነች ማለትህ ነው? »

«በደንብ ነዋ»

«ሁሉም ይሁን» አለኝ አበበ «በል ደብዳቤውን እንጻፍ» ብሎኝ እየተዳዳን በወረቀት ለሚያብዱ ጨርቅ የሚያስጥል ጻፍን፤ ከደብዳቤው ጋር የሚሰጣትም የወርቅ አምባር ገዝቼ ሰጠሁት።

አበበ ሁሉንም መስጠቱን ማክሰኞ ማታ ለኔ ለጌታቸው ነገረኝ፤ ረቡዕ መልሱን ጠይቋት አላሰናዳሁም ማለቷን ነገረኝ፤ ሐሙስ ማታ እቤቱ ብሔድ የሰጠችውን ደብዳቤ ሰጠኝ፤ አከነብኩትና «እህእ አበበ ታዲያ አላፈርክም? » ብለው ብለው ሲጃራውን ለኮሰና «ውሸቷን ነው» አለኝ፤

«እንዴት? » ብለው ከፎቴው ላይ ቁጭ ብሎ እግሩን አጣመረና ለጠጥ ብሎ «ስትግደረድደር ነዋ» አለኝ፤ እፊቱ እንደ ጅብራ ተገትሬ «ሰያን ነህ» አልኩትና «እንድንጣላልህ ትፈልጋለህ» በለው የአፉን ውስጥ ጭስ ወደ ጣሪያው እፍ ብሎ ፈገግ አለና» ደሞ ልጻፍላትና? » በለኝ «በደስታ! ብትፈልግ ደግሞ የምትሰጣት ሌላ ስጦታ ገዝቼ እሰጥሃለሁ» ብዬ በማርታ መኩራቴን በግንባሬ ላይ አስነበብኩት።

አበበ ወረቀት ሲያመጣ ወደ ጽሕፈት ቤቱ እየሔደ ከምግብ ቤቱ ሲደርስ ዞር አለና «መልካም፤ ማርታን ከቤቴ አምጥቼ እዚያች አጠገብ እተቀመጥኩባት ፎቴ ላይ እንገቷን አቅፈ ተቀምጬ ባላስላይ ምን አለ አበበ በለኝ» አለኝና እንደ ዛተብኝ ሔዶ ወረቀትና ብዕር ይዞ ተመለሰ።

ለደብዳቤዋ መልስ ለሁለት ቃሉን እያዋጣን ጻፍንላትና አንዲት ጥሩ ሰዓት ገዝቼ እንዲሰጣት ሰጠሁት፤ ለሁሉም መስጠቱን ነገረኝ።

መልሱዋ በሦስተኛው ቀን መጣ፤ ደብዳቤዋን አንብቤ «አሁንስ አልተረታህም» ብለው ሲጃራውን እያቦነነብኝ «ውሸቷን ነው» አለኝ፤ «አንተ ሰው ምን ማለትህ ነው? » ብለው የማገውን የትንባሆውን ጭስ አንገሩን አቀርቅሮ እግሮቹ መሐል ከነፋ በኋላ እንዳቀረቀረ «እኔን አስጠልቷት እንደሁ እንጂ አንጃ ከዚያ ከለቦጫም ጋር እንኳ በታኑስ መኪናው ሽር ትል ነበር» አለኝና እንዳቀረቀረ ሠርቆ አይቶኝ ቀና ብሎ ቁጭ አለ።

«የቱ ለንቦጫም በል? » ብለው ሳቅ አለና እግሩን አነባብሮ «ወንድ ወሰን» አለኝ፤ ግንባሬን ኮስትሬ የቀኝ እጄን የሌባ ጣት እየወዘወዝሁ «ፈጽሞ አሁን ደግሞ የባሰ ዋሽህ» አልኩት አበበ በፎቴው ላይ ጋደም ብሎ ያነባበረውን እግሩን እያወዛወዘ «አንተ ዋሽህ የምትለኝ የወንድ ወሰንን ነው፤ ኃይሉስ ቢሆን ምኗ መሰለህ? »

አለኝ፤ ጐብደድ ብዬ ባንድ ጐኔ ተቀመጥሁና «ዓይነ ሽንጋራው? » ብለው ዓይን ዓይኔን እያየኝ «ታዲያሳ» አለኝ።

እንደ ገና ተመቻችቼ ሙሉ ለሙሉ ተቀመጥሁና «ኦ አበበ ልክ አይደለህም - አንዴ እንኳ ሰናይት ፓርቲ ላይ አይታው ይሔ ሰውዬ ያቅለሸልሸኛልና ባንተ ከለላ ልሠወር ብላኛለች» አልኩት፤ አበበ ትንባሆውን ማገና «አያሌውስ? » ቢለኝ «የቱ አያሌው? » አልኩት፤ ተንጠራራና ሲጃራውን ከመኮስተሪያው ላይ እያጠፋ በተጨነቀ አስተነፋፈስ እየተነፈሰ «የፊታውራሪ ሰጠኝ ልጅ» አለኝ፤

እንደ ጦጣ ሽፋሌን አሻቅቤ «ሽሉ? » ብለው «ባንተ ሲጫወትብህ ምን ሽል ነው» አለኝ፤ ነደደኝና ከመቀመጫዬ ብድግ ብዬ «አበበ አንድ ቃል ልንገርህ» ብለው አቋረጠኝና እንደተቀመጠ አንጋጦ እያየኝ «ምን ትለኝ? » አለኝ።

ሁለቱንም እጆቼን ከኪሶቼ ከትቼ «ከዛሬ ጀምሮ በኔና በማርታ ጉዳይ አትግባ፤ ልታገባት ከጅለህ እንደሆነ» እንዳልኩት አበበ አሁንም አቋረጠኝና አሻቅቦ እያየኝ «ይቺን ሸርሙጣ ምን አገባታለሁ፤ ላንተው

ሲነደኝ» አለኝ፤ የቀኝ እጄን ከኪሴ አውጥቼ ሊባ ጣቴን እየወዘወዝኩበት «ሁለተኛ ደግሞ አትስደባት፤ ብትፈልግ ጓደኝነታችንን ልንሰርዝ እንችላለን፤ እንዲያውም ደህና ሁን» ብዬው በንዴት እየተራመድሁ ቤቱን ጥየለት ወጣሁ።

//-----//

ረቡዕ ዕለት እባንክ ገብቼ ካቶ ማርቆስ ደስታ ጋር ተጨዋውቼ ብቅ ስል ባንዲት ሺቭሮሌት መኪና አንድ ለንቦጩ ረዘም አፍንጫው ደፍጠጥ ማጅራቱ አበት ያለበት ሽንብራ ጠጉር ጥላሸት ቆዳ ወጣት ካንዲት ሽክ ካለች ወጣት ጋር እያወራ ሲያልፍ አየሁ።

መቸም ዘማች ባለው ነውና የሚሰለፈው በሴይቼንቶ ሾፍሮሌታቸው መከተል ጀመርኩ፤ ደረስኩ፤ ለተንኮሉ የሴይቼንቶው ነጂ ለጉራ አልተሳሳትኩም፤ እኔም ደንገጥሁ እስዋም አመድዋ ቡን አለ፤ ብቻ የነሱ መኪና መስተዋቱ ተዘግቶ ነበርና ቡን ያለው አመድዋ አልደረሰብኝም።

እቤቴ ሔጄ ተኛሁ ተቃጠልኩ፤ ደበንኩ በጠቅላላው እርር ክስል ብቅት አልኩ፤ ኪዎስክ መክፈቱ ያልተስማማት ደህና ገረድ ተገኝታ ብታያይዘኝ ከአልቦ እስከረጃው ቡና የማስከትም ይወጣኝ ነበር።

«የለም እንዴ? » ስትል የማርታን ድምፅ ሰማሁ ላብ አሰመጠኝ፤ ፈላብኝ፤ ልቤ አለመጠን ከረቦ ይመታ ጀመር፤ ሰልፈኛ ቢያገኝ ላንድ ሻለቃ ጦር ማራመጃ ይበቃ ነበር ከመኝታ ክፍሌ ስትገባ ሽፍንፍን አልኩባት ካልጋዬ ላይ ቁጭ ብላ «ጋሽ ጌቱ? ጌትዬ? ስማ እንጂ» ብትለኝ ብርድ ልብሴን እንደተሸፈንሁ «ዞር በይ አንቺ ሸርሙጣ» አልኳት።

ጋደም እንደማለት ብላ ክንብንቤን ገልታ በሁለት እጅዋ አንገቴን አቅፋ ቀና አድርጋ ግንባሬን ሳመችኝ፤ እኔም ፊቴን እንዳስከፋሁ ዓይኗን ሳላይ «ያን ጥልማኮስ ሌንቦራም በሳምሺበት አትሳሚኝ» ብላት ጉንጬዋን ነፋ አድርጋ ድምፅዋን አጐርንና «ኧረ አበስኩ ገበርኩ በል እቴ ምኔ መሰለህ» አለችኝ።

ዓይኔን አቅንቼ እያየኋት «ምኔ ነው ልትይ ነው? » ብላት ግንባርዋን ኮስተር አድርጋ «እንግዲህ እናንተ ወንዶች ሁለን መጠርጠር ነው? » ብላ

ራስዋን ነቀነቀች እኔም በመቆጣቴ ላሳያት ግንባሬን ኮስትሬ «ምንሽ ነው? » አልኳት፤ እስዋም አልጋውን ተመርኩዛ ጉንጪን ደግፋ «ለመሆኑ ጌቱዬ? ስንቱን መሐላ ምየልህ ትጠረጥረኛለህ» እልችኝ አሁንም ግንባሬን እንደኮሰተርኩ «ሰውዬው ምንሽ ነው? » አልኳት ማርታም የራሴን ላይ ጠጉር እየነቃቀሰች በለሰለሰ አንደበት «ለምን አታምነኝም? » አለችኝ አሁንም እንደነበርኩት ሆኜ ያንኑ ቃል ደግሜ «ሰውዬው ምንሽ ነው? » አልኳት።

ማርታ ጠጉሬን መነቃቀስዋን ትታ በሁለት እጅዋ ሁለቱን ጉንጮቼን ይዛ በአዘነ አነጋገር «በቀደም እማማ እንኳ አልነገረችህም? » አለችኝ ቀና ብዬ ዓይኗን አየሁና «ምን ብለው? » ብላት እንደ ነበረች ሁና ጉንጩን እንደያዘች ራስዋን እየነቀነቀች «ወንድማችን ከውጭ አገር ገባ አላለችህም? » ብልተኝ በቅያሜ አነጋገር «ታዲያስ» አልኳት «እሱ ነዋ» አለችኝ «ትምያለሽ? » ብላት «ኧረ ያጥፋኝ እቴ» ብላ ቀና አለች፤ እኔም ዓይን ዓይኗን እያየሁ «ለምን ታዲያ በትምህርት ሰዓት ወጣሽ? » ብላት ጉንጪን ነፍታ በኩርፊያ አነጋገር «የትዬ ወይኒቱን ቤት አያውቀው ስለ ነበር አሳዩኝ ብሎኝ ነው፤ አሁን እንኳን ከዚህ ያደረሰኝ እሱው ነው፤ እሺ ሌላ ነገር ቢሆን ከዚህ ያመጣኝ ኖርዋልን? ተው ኧረ ተው ተው ጌታቸው? » አለችኝ ራስዋን እየነቀነቀች።

እንዳትቀየመኝ በልቤ እየሠጋሁ ፈገግታና ኩርፊያ በተቀላቀለበት ሁኔታዬ «ስሙ ማነው? » ብላት በፈጠነ አመላለስ «ከበደ» አለችኝ «ወንድምሽ ነዋ? » ብላት «ሙት ስልህም አታምነኝም እንዴ? » ብላ ቆጣ አለች። አሁንም እንዳትቀየመኝ እየሰጋሁ ፈገግ ብዬ «ጠረጠርኩሽ» አልኳት ማርታ ፈገግታዬ ዕጥዋን መልሶላት እንደ መሳቅ እየከጀላት እንደልፊያም እየሞከረችና «ይልቅ አትጨቅጭቀኝ፤ እልፍ በልና ልተኛበት ለራሴ ደከሞኛል» አለችኝ፤ በውነቱ ከሴት ተጣልቶ መታረቅ እንደ አዲስ ያረጋልና ልቤ የደስታ ድልቅታውን እያደመቀ «ከወዲያ ወገን እለፊና ተኚ» አልኳት።

ከማርታ ጋር ተራረቅን፤ በከንቱ መናደዴም ቆጨኝ፤ ማርታም ከከበደ ጋር አስተዋወቀችኝ፤ እኔ ሥራ በሚበዛብኝ ጊዜም ከበደ ከተማሪ ቤትዋ እቤትዋ ያመላልሳት ጀመር።

አለቆቼ አዘዙኝና ወደ ጐፋ ሔድኩኝ፤ የጐፋ ጉዞዬ ሁሉ የኀዘን ነበር፤ እንኳን የምበላውን የምጠጣውንም አላውቀውም ነበር፤ ጉሮሮዬ እንኳ የምጠጣውን ውሃ አላወርድ ብሎ ተዘጋ፤ ውሀ በጠጣሁ ቁጥርም እንደ ዶሮ ለማንጋጠጥ ጥቂት ቀረኝ።

ከማርታ ጋር በጣም እንዋደዳለን፤ ማርታ የፍቅር ከረጢት ናት፤ ማርታ ታይታ የማትሰለች የባሕር ላይ ጨረቃ ናት፤ ማርታ የማትጠገብ የወደማታ ፀሐይ ናት፤ ማርታ የሰውነቴ ማንቀሳቀሻ ደሜ ናት፤ ማርታ የምታጓጓ የገደል ላይ እንኮይ ናት፤ ማርታ በሐሳብ አብራኝ የምትጓዝ የስንቄ ከረጢት ናት።

ስናፍቃት ከረምሁ፤ ውል ስትለኝ ከረመች፤ ሥራዬን እንደ ነገሩ አደፋፍቼ በቶሎ ወደ አዲስ አበባ ለመሔድ ተነሣሁ፤ መንገዱ እራቀኝ፤ እስታያት ቸኮኩ፤ እስታገኛትም ብርክ ያዘኝ።

አዲስ አበባ ገብቼ ከአውቶቡስ ላይ ልወርድ ስል ያ ቀልቃላ ሰይጣን አበበ ግጥም አለኝ፤ የአበበን ጓደኝነት ካንጀቴ ቆርጬ ትቼዋለሁና ላነጋግረውም አልፈለግሁም።

ጠጋ አለኝና ባዘነ ወይም ባኮረፈ መልክ «እንኳን ደህና መጣህ» አለኝ፤ በፊቴም በልቤም ያለችው ማርታ በመሆንዋ ነገር አዋሻኪውን አበበን ላናግረው አልፈለግሁም፤ ማርታን ደስ ለማሰኘት ከጐፋ ያመጣሁላትን የባሕል ዕቃዎች የያዘውን ሻንጣዬን ይዤ ስወርድ አበበ ቀበል አለኝና «ቁርጡን ተረዳኸው አይደል? » አለኝ፤ «የምኑን? » ብለው «የማርታን» አለኝና በጐድን አሻቅቦ አየኝ፤ «ምን ሆነች? » ብለው «አገባቻ» አለኝ።

በነገሩ ፍጹም አለማመኔን ላሳየው አፍንጫዬን አኮማትሬ «ወይድ አንተ መናጢ» ብዬ ወደ ማዶ አይ ጀመር፤ በግራ እጁ የያዘውን ሻንጣዬን ከመሬት አሳረፈና «አልሰማሁም እንዳትለኝ ብቻ» ቢለኝ «የምኑን» አልኩት፤ እስክስታ እንደሚወርድ ትከሻውን መታና «ቂል የማግባታዋን

ነው» ብሎ አንገቱን አወላግዶ በጮለጮለ አስተያየት አየኝ እኔም እሱው እንደሆነው ሆኜ «የምትለኝ አልገባኝም» አልኩና አንገቴን ወደ ጐን ሸቆርኩት።

ከዚያ በኋላ የመርካቶ ሊስትሮዎችና ኩሊዎች ሽቃዮች ሁሉ ከበውን ለጉድ እስኪያዩን ድረስ እንለፋለፍ ጀመርን፤ «የምልህ አገባች ነው« ቢለኝ «ሙት በለኝ» አልኩት።

«ሙት»

«ሙት? »

«ሙት»

«ሙት? »

«እስቲ እንዲያው ሙት በለኝ»

«ሙት»

«ሙት? »

«አበበ በጄ በልተሃል እስቲ ሙት በለኝ»

«ሙት አልኩህ»

«ማንን»

«ከበደን»

«ከበደን? »

«አዎ ከበደን»

«ወንድሟን»

«የመቼውን»

«ምነው ወንድሜ ነው ብላኝ»

«ስታታልልህ ነዋ»

«ሙት በለኝ»

«ሙት»

«መቼ»

«ትናንት»

«ሙት በለኝ? »

«ሙት»

«ወይኔ ጌቱ»

«እኔኮ ሰምተህ የመጣህ መስሎኝ ነበር»

«በቃ ተወኝ»

ከአበበ ጋር በቀጥታ ከነ ከበደ ቤት ሔድን፤ ግርግር በዝቷል፤ ጥቋቁር ሱሪ ታጥቀው በነጫጭ ሸሚዝ ብቻ የሆኑ ጐረምሶች ወጣ ገባ ይላሉ፤ ፈረስ የሚያስፈትን ዳስ ተጥሏል፤ የዳሱን ውጪና ግቢ በአበባ አምሮአል።

እንደደረስን ዘበኛውን «አቶ ከብደ አለወይ? » አልን፤ «አሉ» አለን፤ «እባክህ ጥራልን» ብንለው ሳቀና «ታሾፋላችሁ መሰለኝ» አለን፤ ደሜ ፈላ፤ ነደደኝ አወቅሁት፤ ገባኝ ተረዳሁት አበበ መለሰና ለዘበኛው «ምነው ደህና አይደለሞይ? » ቢለው «ዛሬ ሙሽራ ናቸው» አለን።

ዓይኔን ጠበብ አደረኩና ጭንቅላቴን አዝምሜ በንቀት «ማንን ነው የሚያገባው» ብለው ዘበኛው ጉርጥርጥ ዓይኑን እያጉረጠረጠብኝ፤ «ወይዘሮ ማርታን» አለኝ፤ አበበ ቀበል አለና «ማራታ የማልጅ ናቸው? » ቢለው ዘበኛው እንደ ማፈር አንገቱን አቀርቅሮ ቀና አለና አበበን «በጣም የታወቁ የትልቅ ሰው ናቸው» አለው፤ ደሜ ፈልቶ ቆጣ አልኩና «የአባትዋ ስም ማነው? » ብለው «አጉቶ ነው መሰለኝ» አለኝ።

ምንም ሳልናገር ወደ ኋላዬ ምልስ ብዬ ከመጣንበት ከአበበ መኪና ልገባ ስል አዎ እዚህ ድረስ ይታወሰኛል ከዚያ በኋላ ልሙት፤ ልኑር ልሂድ፤ ልቀመጥ ሰው ልሁን ድመት፤ ማርታን ልግደል ከበደን ልደብድብ አላውቅም

//=//

ሲስተር ብስኩት በፎጣ ውሀ እየጨመቀች ግንባሬ ላይ ታደርጋለች፤ አንደኛው እጅጄ በጠፍጣፋ እንቸጥ ላይ ታብቶ በጠርሙስ የተሰቀለ ውሀ (ግሉኮስ) በመርፌ በክንዴ ይንቆረቆራል።

እናቴ፤ አበበና ሌሎችም አሉ፤ ማርታ የለችም አበበን ብጠይቀው አሁን ሔደች አለኝ፤ ሲሻለኝም በጥሞና ሁሉንም ነገር አስረዳኝ፤ ነገሩም ገባኝ፤ ከሆስፒታልም ወጣሁ፤ ስለደረሰብኝ ታሪክ ጓደኞቼ ሁሉ አበራረዱኝ፤ ለማረሳሻም በማርታ ቦታ የሻረግን ተኩልኝ፤ ማርታን ረሳ አደረኳት፤ የሻረግ ባስለጣጠኗ ባለባበስዋ ደስ ብትለኝም የምታ ባለቀይ መብራት በመሆንዋ ቅር ትለኝ ነበር፤ በቅጠሉም በገለባውም ብላ መቼም ማርታን አስረሳችኝ።

አንድ ቀን ማታ ተኝቼ የማርታ ነገር ታወሰኝ፤ ወረቀት ልጽፍላት ብዬም አልጋዬ ላይ እንደሆንኩ በግራ ጐኔ እንደተጋደምኩ ጻፍኩላት፤ «……ዛሬ ማርታ እልሻለሁ፤ ወይዘሮ ግን አልልሽም……ከዳሺኝ……ከምስር መልቀሚያ ሰዴድሽ እንዳነሳሁሽ ረሳሽኝ……አታለልሺኝ…….መስሎኝ እንደ ነበር ወንድምሽን አገባሽው…….ምነው ያን ጊዜ አበበ አንባር ሲሰጥሽ ለምን ጌቱ ነው ወርቁ አልሽው?......ሰዓት ሲሰጥሽ የቀን መቁጠሪያዬ ጌቱ ነው ለምን አልሺው?.......ከዳሺኝ ማርታ……ከዳሺኝ በእርግጥ ከዳሺኝ ምነው በአበበ ጊዜ በቀጨሽ፤……ይድላሽ…….የፍቅር አማልክቶች ይፍረዱ……ውሻ ነሽ…….ጠላሁሽ፤ እስስት ነሽና ቀፈፍሺኝ…….» የሚሉ ቃላት በላኩላት ደብዳቤ ላይ ነበረበት። እውነትም የወደድኳት ያህል ጠልቼአታለሁ፤ ያምረኝ የነበረው ሁኔታዋም አስቀይሞኛል።

አንድ ቀን ደብዳቤ ደረሰኝ፤ ፖስታውን ብቀደው የማርታ ጽሑፍ ነው፤

«……ወዳጄዋ መሠልጠን ነው፤ እስክወድህ ወደድኩህ፤ ስጠላህ ብጠላህ አትፍረድብኝ……በዚህ ጊዜ አንተም ብትሆን ልትለውጠኝ ትችል ነበር፤ ነገር ግን ሳታረገው አረኩት፤ በዚህም አይከፋህ፤ ሁሉም መብት አለው፤ ነፃ ነን።»

«……ባልከኝ ሁሉ አጥቼብህ ይሆናል፤ አንተም በአበበ ስትፈትነኝ አጥፍተሃል፤ አበበ ጓደኛህ መሆኑን አውቅ ነበር፤ ልታታልለኝ እንደሞከርክ ቃሌን በጓደኛህ በአበበ ላኩልህ፤ እርሳኝ።»

«……ከበደም ካጨኝ ቆይቷል፤ ካንተ እኩልም ያስጌጠኝ ነበር፤ አየሁ እሱ ደግሞ የትላልቅ ሰዎች ወገን ነው፤ ብዙ መንጠላጠያ ያለው ወርካ ነው፤ እርሳኝ፤ ሚዛን ሆኜ ወደ ከበደ ደፋሁ፤ <u>መልካሟን እንዲያጋጥምህ</u> እመኝልሃለሁ።

# <u>ምዕራፍ ፪።</u>

«የባልና የሚስት መሸመቻው ፒያሳ ነው» ሲሉ እሰማ ነበር፤ በእርግጥም ፒያሳ የደራ ገበያ ነው፤ የፒያሳ ገበያ የሚደራው ከአሥር ሰዓት ተኩል ጀምሮ ነው።

እኔም ገበያው ከደራበት ሚስት መሸመቱ የተሻለ መሰለኝ፤ በውነትም ጥሩ ሐሳብ ነው፤ ስለዚህ ገበያተኞቹ በሚበዙበት ጊዜ እኔም እንዳቅሜ እንደሌሎቹ ሁሉ ሽክ እልና ብቅ እል ጀመር፤ አንድ ቀን ለታካንድ ሱቅ ገብቼ ስወጣ ሦስት ሆነው ሲቀሽሩ ከፊቴ አየኋቸው።

እነሱ ሲሔዱ እኔም ስከተል አራዳውን አራት አምስቴ ያህል ዞርነው፤ ፓሪ ሞድ የለበሰችው ከወደኋላዋ አጐንድራ ደስ አልልህ አለችኝ፤ ደግሞ ያደረገችው ሹል ጫማ ስለ ነበረ ጉልበትዋ እጥፍ እጥፍ እያለባት ቃሊብዋ (ፎርሟ) አስቀየመኝ፤ ከጉልበትዋ በላይ ዝንጉርጉር ቀሚስ የለበሰችው ቋንጃዋ አመድ መስሎ ስላየሁት ናቅኋት፤ ደግሞም ያ ሁሉ ቅልጥሟ ባዶ በመቅረቱ ምን ልበል ብቻ አንድ ነገር መሰለችኝና ጠላኋት፤ ያንደኛይቱ አካሔድ ግን ገና ሰበር ሰካ ነው፤ እንደገመትኳት የከተማው እንግዳ መጤ ናት።

ሦስቱም አጊጠዋል፤ በነሱ ቤት አምረዋል፤ ተውበዋል ይህ ሁሉ ሲሆን አመራረጤ ከወደኋላቸው ብቻ ስለ ነበር ፊታቸውን ለማየት ፈለግሁ፤ ፈጠን እያልኩ ተራምጄ አለፍ አልኳቸና ሰው እንደሚጠብቅ ቆሜ ሳሳልፋቸው ባያቸው ባለፓሪ ሞዷ አፍንጫዋ ድፍጥጥ ያለ፤ ከንፈርዋ ከጉርሻ የሚተርፍ ሆኖ በዚያ ላይ አፈጭቃ፤ ግንባርዋ ያፈጠጠ፤ ዓይንዋ ያጐረጠ፤ ጡትማ ለምልክት አልሠራባት፤ እንዲያውም ከኔው እኩል ሳይሆንም አይቀር ዋሽህ አትበሉኝና ባፍንጫዋ ቀዳዳ ጉሮሮዋ ወለል ብሎ ይታያል።

ያቺ ደግሞ መንቃራዋ ከአፍዋ ቀድሞ የዝሆን ኩንቢ የመሰለ፤ ከንፈርዋ የሳሳ የውሻ ምላስ የመሰለ፤ ደሞ እኔ እንጃላት እናትዋ በዘነዘና ብላታለች መሰለኝ ግንባርዋ ላይ ያለው ጉድጓድ የሺሊንግ ጠላ ያቁራል፤ እግረ መንገዱንም አሣ እንኳ ቢያረቡበት ያረባል፤ ሆድዋ ዝርጥጥ ብሎ ሦስት ያረገዘች ድርስ እርጉዝ ትመስላለች፤ ብቻ እርጉዝ ሳትሆን አትቀርም፤ ታዲያ ቢረገዝስ ያን ያህል ሆድ ምን ይሠራል? ልጆቹ ሲወጡስ ምን ይሞላል? ጤፍ እንጀራ ወይስ ጭድ?

ያቺ ደግሞ ቀረፈፍዋ ባላገር ቢጤ ገና ስታየኝ ፍዝዝ አለችና በሁኔታዋ ልሙትብህ አለች፤ እኔ ደግሞ የምትወደኝን እንጂ የምትሞትብኝን ስለማልፈልግ ተወት አደረኳት ከጓደኞቹ እስዋ ትሻላለች፤ የፒያሳው ዕቃ እንዲህ ዓይነት በመሆኑ ገረመኝ።

ካለፉኝ በኋላ አበባ ከሚሸጥ ሱቅ ገባሁና አንዲት ጽጌረዳ ገዛሁ፤ ቶሎ ብዬም እነኛው ልጆች ላይ ደረስኩባቸው፤ ግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ስንደርስ ደብለቅ አልኳቸውና በድንገር «ይቺን አበባ ማናት በስሟ የምትለውጠኝ? » አልኳቸው።

ያቺ ባለ ፓሪ ሞድዋ ቶሎ አለችና «አልማዝ እባለሁ» ብላኝ አበባይቱን ተቀበለችኝ፤ እኔም በሆዴ «መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ የተባልሺው አንቺ ነሽ? » አልኩና ጭጭ አልኩ።

ጆን ሜሊ መንገድ ስንደርስ አልማዝ ከኁልቱ ጓደኞችዋ ተለይታ አቀበቱን ከኔ ጋር ተያያዝነው፤ መቼም በአዲስ አበባ በፍቅር ርካሽ ነውና ወዲያው ተዋደድን፤ ትኩር ብዬ በጣለብኝ ፍቅር ዓይን ባያት ኩንስንስ

ያለች ሞንዳላ ልጅ ኖራለች፤ የአፍንጫዋ ማስደሰት የከንፈርዋ ማማር፤ የዓይኗ የብር ጓል የመሰለ ድንቡሽቡሽ ያለች ልጅ ናት። እንዲያውም የሐረርጌ ቆቱዎች «ትንቡሼ ገላ ነይ» እያሉ የሚዘፍኑላት እስዋ መስለችኝ፤ ጥሩ ሸንቃጣ ወገብ እንዝር ልጅ ነች።

አንገቷን አቀርቅራ ጣትዎችዋን እያሻሸች «እንዲህ አብረን ስንሔድ ስሜ ይጠፋል» ብትለኝ ኮራ ብዬ ወደ ቀኜ እያየኋት ፈገግ አልኩና «እንዳይጠፋ በመሐረቤ እቋጥርሻለሁ» ብያት እየተሳሳቅን ጥቂት ሔድንና ዝም አልን።

ቀና ብላ ዓይታኝ ተሽኮርምማ አቀረቀረችና በኊለደፈ አነጋገር «ስሜን እንደወሰድክ ስምህን ስጠኝ» አለችኝ አሁንም ፈገግ ብዬ ኪሶቼን በእጆቼ እያራገፍሁ «ላለመውሰዴ ልመርመር» አልኳት፤ እግርዋን ከመሬት ጋር እየተጐተተችና አካሔድዋን ወደ ፊትዋ ደፋ ደፋ እያደረገች በዕረፍት አነጋገር «ጠበቃ ገዝተን ሳንጣላ መስማማት ብትፈልግ ላዋሰኩህ ስሜ ስምህን ክፈለኝ» ብትለኝ የግራ እጅዋን እጄ ጨበጥ አድርጌ «ካሳሽን አልችለውምና እናቴ የሁሉም ሁሉ አንተ ነህ ጌታቸው ብለውኛል» አልኳት።

ፈገግታ ባለው አስተያየት ቀና ብላ እያየችኝ «በኔው ነው እንዴ ጌታ የሆንከው? » ብትለኝ «ኖ አይደለም፤ በብር» አልኳት፤ እስዋም በማሽሟጠጥ «ዲንቄም እቴ» ብላኝ አፍንጫዋን አጨማዳ ፊትዋን ወደ ቀኟ አዞራ መለሰችው።

የደከማት መሰለኝና «ሶሪ አልሙ አደከምኩሽ» ብላት «ልቤን አወለከው እንጂ» አለችኝ።

«ዋሸሽ እንጂ ደረትሽን እንኳ አልቀደድኩትም»

«ያልቀደድከው ስላልፈቀድኩልህ ነው፤ ግን ተሰውረህ ገብተህበታል»

«ልውጣልሽ? »

«ተቀመጥበት አከራይቼሃለሁ»

«ኪራዩሳ»

«መሳ ለመሳ»

«አንድ ነገር አልሙ - የጣሳ ምግብ ልግዛልሽ? »

«አብረን ልንበላው ምን ከፋኝ»

«ድፍን ወይስ ክፍት? »

«ማንም እንዲከፍተው ስለማልፈልግ ድፍን? »

«ድሮ ልጆች ሆነን ኩኩሉ እንጫወት ነበር፤ አንቺሳ»

«እኔም»

«እምዬ ማርያም ላይ ትተኚና ምን እንቁላል? ሊሉሽ ምን ትይ ነበር? »

«ድፍን»

«ልክነሻ»

«በደንብ ነዋ»

«ልጅዬ ይሄ የያዝሺው ቦርሳ ይከፈተአል? »

«ቁልፉን ላገኘ ነዋ»

«ከየት? »

«ከልቤ»

«ቁልፉ ደም ነው ማለትሽ ነው»

«ለተዘጋ ነገር ደግሞም ለታሸገ - ባክህ አታድክመኝ»

ከአልማዝ ጋር ብዙ እየተነጋገርን አራዳውን ዞርነው፤ በኋላም ለቅዳሜ ፱ ሰዓት እዚያቹ ቦታ እንድንገናኝ ቀጠረችኝና ዱካ ሱቅ በራፍ ላይ ተለያየን።

//=//

«አልማዝ ቀልዱን ተይውና እውነቱን ንገሪኝ ብላት የውስጥ ልብስዋን እንደለበሰች ከፊት ቆመችና «በፈጠረህ ጌታ ይሁንብህ፤ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ መሳቂያ አታድርገኝ» አለችኝ።

በከፉ ዓይን እያየኋት ግንባሬን ኮስትሬ «ይሔን ከሽከሽ ተይውና ተናገሪ እዛሬይቱ ቀን ከመድረሳችን በፊት እንኳ ምን ያህል እንድከሰርኩልሽ ታውቂያለሽ እስከ ቅድም አልቆጨኝም፤ አሁንም አልማዝ» ብዬ ገና ሳልጨርሰው ከጉልበቴ ሥር በርከክ አለችና ራስዋን አቅንታ እንባ ባቀረረ ዓይን እያየችኝ «የኔ ጌታ አፈር ድሜ ስበላልህ» አለችኝ።

በጉልበቴ ደረቷን ብዬ ፈነገልኳትና «ያኔ ነበር መለማመጥ ማነው ነው የምልሽ? » ብዬ ዓይንኔ ባፈጥባት ከዚያው ከተጋደመችበት ቀና ብላ በግራ ክርንዋ መሬቱን ተደግፋ እያለቀሰች «እባክህ ሰው ይሰማሃል ቀስ በል» ብላኝ ብድግ ብላ ቆመች፤ እኔም አፌን አጣምሜ በቁጭት «ገና አውጅልሻለሁ» ብዬ በግራ እጄ በቃሪያ ጥፊ አንዴ ብለትማት ጮኸችና እግሬ ሥር ክብልል አለች፤ ወዲያውኑ ፩ኛ ሚዜ ያደረኩት ወልዱ ከጭፈራውና ከዘፈኑ መሐል ወጥቶ ከኛ ክፍል ጥልቅ አለና ዓይኑን አፍጦ እጆቹን ዘርግቶ «ምነው ምን ነካህ» ቢለኝ፤ እኔም ዓይኔን አፍጥጬ በኃይል ሲቃ እንደያዘኝ «ተወኝ ተወኝ፤ ብቻ» አልኩት ወልዱም ጉዳዩ ገባውና ከጀመሪያው ሁኔታው መለስ ብሎ «ታዲያ ቢሆንስ ሰው ትገላለህ እንዴ? » ቢልኝ አልማዝን እስሬ እንደ ተኛች አንዴ በርግጫ ደለዝኳትና «ድብን ትበል ይቺ መንቃራ ጋለሞታ አልኩት።

ወልዱ ነገሩን ለማብረድ ብሎ እጄን ሳብ አደረገኝና በለስለሰ አነጋገር «በል ና አሁን እንውጣና ዘፋኞቹ ዘንድ ሔድን እንጫወት» አለኝ፤ የያዘኝን እጄን እንደያዘው በረጋ ሕሊና «ወልዱ በናትህ በእማሆይ አመተ ማርያም ይሁንብህ፤ ባባትህ በደጃች አመዴ አጥንት ይዤሃለሁ፤ አንተ ብቻ ከዚህ ክፍል ውጣ» ብለው።

«ለምን? » አለኝ

«ይቺን ሐርሎት ላሳያት»

«ድሮ የቀረውን? »

«ለምን ይቀራል? »

«ቀራ»

«ይሔ የናንተ ወሬ ነው፤ እነሱ የትም እሽከም እያሉ ይከርሙና አንገታቸውን ቅልስልስ እያረጉ በቧል አግባኝ ይላሉ፤ ታዲያ ከሥሬ እፍታዬ ተበልቶ እንዲያው እንዲያው እንዲችው ዓይኔን አፍጥጬ ልቅር? » ብለው አንገቱን ወደኔ ዞር አድርጐ «ታዲያ ምን ትሆን» አለችኝ።

«ሰውዬውን ትንገረኝ» ብለው

«ብትነግርህ ምን ይሆናል» አለኝ።

«ይሄን ዶሮ የሚፈጀውን የመንደር ምጥማጥ ማወቅ እፈልጋለሁ»

«እባክህ ጌታቸው ይቅርብህ»

«ስማኝ ወልዱ - እዚህ ላለው ዘፋኝና አጨብጫቢ ሁሉ በአዋጅ ተናግሬ ቁጭቴን ተወጡልኝ ነው የምለው፤ የምትነግረኝ ከሆነ በጨዋ ደንብ ያው ባንተ ፊት ትንገረኝ እምቢ ካለች ያው ነው» አልኩት።

ባፈር በመሬት ትርበትበትና ወልዱ ከኋላው እየተርበተበተች ወደ ቆመችው አልማዝ ዞር አለና «የምትጐጂበት ነገር የለምና ንገሪው» ቢላት ያን ለንቦጭዋን ቁልቁል ለቃ ጣቶችዋን በጣቶችዋ እያፍተለተለች አቀርቅራ፤ «ጋሼ ወልዱ፤ አንተ አትሒድ እንጂ እነግረዋለሁ» አለች።

«በይ እሱው ባለበት ንገሪኝ» ብላት

«ዕድሜዬ እኮ ትልቅ ነው» አለችኝ

«ታዲያስ? »

«ጠፋአ»

«ማን አጠፋው? »

«አውቆ ነዋ»

«እኝኝዋ አውቆ ነዋ ትላለች፤ የነማን አውቆ እንደጠፋ ያንቺ ይጠፋል? ትናገሪ እንደሆነ እውነቱን ተናገሪ» ብዬ እቅጭዋን ነገርኳት።

«እሺ እናገራለሁ» አለችኝ

«እንዲያውም በይ ማይ»

«ምን ብዬ? »

«ውሸት ብናገር ጊዮርጊስ አይለመነኝ በይ»

«አይለመነኝ»

«ቃል ለምድር ለሰማይ በይ»

«ቃል ለምድር ለሰማይ»

«ሚካኤል አከላቴን ይገልብጠው በይ»

«እንዴ - ምነው ይሔን ያህል? »

«ይቺ መናጢ አትይም እንዴ» ብዬ በጥፊ ብስታት ከጥፊዬ እንዳጐነበሰች ቶሎ ብላ «ይገልብጠው» አለች።

«ማነው? »

«አክሊሉ ነው»

«የቱ አክሊሉ? »

«የደጃች አረሩ ልጅ»

«ባለ ኦፔሉ? »

«አዎ»

«እንዴት አርጎ? »

«እህእ፤ እንዴት ልበል»

«የት አግኝቶሽ? »

«አገባሻለሁ ብሎኝ»

«ታዲያ ለምን ተወሽ? »

«እናቴ ድህ አታግባ ብለውኛል አለና» ብትለኝ ጣቶቼን እርስ በራሳቸው እያላጋሁ በማስጮህ «ወይኔ ጌቱ፤ የሀብታም ልጆች እንዲህ ይጫወቱብኝ? » ብዬ የአፍንጫዬን ቆዳ አኮማትሬ «ታዲያ ለምን አልከሰሺውም? » ብላት አቀርቅራቅ የጥፍርዋን ዕድፍ በጥፍርዋ እያወጣች «እናቴ ልትከሰው መጥሪያ ብትወስድለት ሦስት ቀን ታሥራ ባማላጅ ተፈታች ነገሩን እንኳ አባባ ሣህሌን ብንጠይቅ የትልልቅ ልጆች ሲከሰሱ ደንቡ ይኸው ነው አሉንና ተውነው» አለችኝ።

«በኋላሳ»

«በኋላ ደሞ ጋሽ አማረ ነው»

«የጐረቤት ልጅ ነው»

«የማን ልጅ»

«ቀን እኛ ቤት ምሳ ስንበላ ለኛ ያሳልፍ የነበረው ጠይሙ ልጅ ነው»

«ያ ብርጭቆ የተሰበረበት? »

«አዎ»

«ለምን እሺ አልሺው? »

«ልጅ ሆነን ሁሉ የከንፈር ወዳጄ ነበር»

«ታዲያስ»

«ታዲያ ስወድሽ ልታመልጪኝ ነው ቢለኝ አሳዘነኝ»

«መቼ ነው? »

«ቆይቷል»

«ይሔ መናጢ የለማኝ ልጅ፤ ያለ ጠረጴዛችን ላይ ጠላ ያፈሰሰው ልጅ ምንሽ ነው? »

«የቱ? »

«አበባውን እንኳ ከፊታችን አንሥቶ የወሰደው»

«አንድ ቀን ከተማሪ ቤት ሲመጣ እናቱ ምሳውን ስጪልኝ ብለው ገበያ ሔደው ነበርና ምሳነው ስሰጠው በግድ ያዘኝ»

«ይዞሽስ? »

«ያዘኛ»

«እኮ ይዞሽስ? »

«እኔ እንኳ ብታገለው አሸነፈኝ»

«አሸንፎሽስ? »

«ልጮህ ስል እንኳ አፌን ያዘው»

«ይዞሽስ»

«በቃ ታዲያ ግፍርት ቢያደርገኝ ወደቅሁ»

«እምን ላይ? »

«በቃ ታዲያ የናቱ መኝጣ አጠገቤ ነበርና እንዲያው ዝርር አልኩ»

«ዝርር ብለሽስ»

«እናቱ እንኳ በኋላ መጡና አልጋው ላይ አርጌው የነበረውን ጌዞ ምን አፈሰሰው አሉ»

«ማን አፈሰሰው አልሻቸው? »

«ድመቷ»

«የምን ድመት? »

«የነማማ ዘብይደሩ ናት»

«የቷ ናት ዘብይደሩ? »

«የጋሽ ለማ እናት»

«እሱስ ምንሽ ነው? »

«ማ? ድመቱ? »

«ኧረ ለማ»

«ታዲያ አንድ ቀን ብቻ ነዋ»

«ምን ያለው? »

«ለዛን ለታው እንኳ እህቱ ትርንጐ አይታን ከረሜላ ገዛላትና አትናገሪ አላት»

«ታዲያ አልተናገረችም? »

«ምነው የእነታባ ማርያም ለታ ለጋሽ መንግሥቱ አልነገረችውም? »

«ምን ብላ? »

«ጋሽ መንግሥቱ እንኳ ታዲያ እንዲህ ሆነሽ ነው የጨከንሽብኝ? አላለኝም? »

«ምን ሆነሽ ማለቱ ነው? »

«ምነው? በቃኝ»

«ሙብረቅ ይሰነጣጥቅሽና ደሞ በቃኝ ትላለች፤ ተናገሪ» ብዬ በወልዱ እግር ሥር አሳልፌ አንዴ በእርግጫ ለኮፍ ባደርጋት «አትማታ እንጂ» አለችኝና በቀኝ እጇ አገጩን ደግፎ የቆመውን ወልዱን የሙጥኝ ብላ

ለንቦጭዋን አለንቡጫ በጒንዋ አየችኝ፤ እኔም ሽቅብ ቁልቁል እያየሁ እንደተናደድሁ «ንፍጣም ሴባ ተናገሪ» ብላት «ምን ልናገር» አለችኝ።

«ብሎሽስ? »

«ማ? »

«መንግሥቱ»

»እህቱ ቤት ወሰደኛ»

«እህቱ እንኳ እነዚያው እድግሱ ላይ ስለነበረች ቁልፍ ተቀብሎ ነው የሔድነው»

«ሔዳችሁስ»

«ከእቱ ቤት ስንወጣ አሰፋና መንግሥቱ ተደባደቡ»

«በምን ምክንያት? »

«በኔ»

«አንቺ ምን አረግሽና»

«አሰፋ ዘሎ መንግሥቱን በጥፊ አለው»

«ለምን? »

«ቀናና ነዋ»

«በማ»

«ምንሽ ኖሮዋል»

«አስተማሪዬ ነበር»

«በኋላስ»

«ፖሊስ ጣቢያ ሔዱ»

«ታዲያ እንዴት ሆኑ? »

«እኔም ተጠርቼ ሔድኩ»

«ምን አሉሽ»

«አሳደሩኝ»

«ማ»

«መቶ አለቃው»

«የት? »

«እቤታቸው»

«ሚስቱስ? »

«አላገባሁም ብለውኛል»

«ከየት አስተኛሽ?

«እኔን እንኳ ላግባሽ ቢሉኝ አንተ ስለ በለጥህብኝ እንቢ አልኳቸው»

«ምነው ባገባሽና በገላገልሽኝ ኖሮ»።

## ምዕራፍ ፫

«ወይሳ ሹታ ቦላን አወይታይ ጊን አዋ ሆአይስ» የሚለውን የወላምኛ አተራረት አንድ ጊዜ ያጐቴ ልጅ ወይዘሪት እጅጋየውሁ ነግራኝ አልረሳሁትም።

ቅቤ ብሆንላቸው ድንጋይ ላይ እንዳሰጡኝ ስላወቅሁ አላገባም ብዬ ማልሁ፤ እንዳጋጣሚ ለማታ ፓርቲ ተጠርቼ ነበር፤ ልክ ቅዳሜ በ፱ ሰዓት ማጌጥ የጀመርሁ ከምሽቱ ፩ ሰዓት ላይ አጋጌጤን ፈጸምኩ፤ ከዚያ በኋላ በየፒያሳአው ላይ ከነተረፈ ጋር ስጫወት አመሻሽቼ ወደ ተጠራሁበት ወደ ሀገር ፍቅር ማኅበር ክበብ ስሔድ አባባ ቶኪቻው አገኙኝና ከኪንግ ጆርጅ ቡና ቤት ገብተን ሚስታቸው ወይዘሮ መደምደሚያ ስለሚያበሳጯቸው

ነገር ሲያወሩልኝ፤ ውርዴ ለውርዴ በጨዋታ ስለሚጣጣም በአባባ ቶኪቻው ወሬ ፈዝዤ የተጠራሁበትን ሰዓት አሳለፍኩት።

አባባ ቶኪቻውን ቶኪቻው የምንላቸው አንድ ዓይናቸው ዕውር ሆኖ ለም ከጠፍ በመሆናቸው ነው እንጂ ስማቸውስ ገብረየስ ነው፤ ስታዩዋቸው ሁለት ዓይን ያላቸው ይመስሏችኋል፤ ግን ሲያታልሏችሁ ነው እንጂ አንዱ የማያይ የበግ ዓይን ነው።

ከአባባ ቶኪቻው እንደ ተለያየን ወደ ፓርቲዬ ወደ ሀገር ፍቅር ማኅበር ሔድሁ፤ ዳንሱ ድምቅ ብሎ መላቅጡ መላ ቅጡ ጠፍቶታል፤ የአዳራሹ መብራት ደብዘዝ ብሏል፤ በከፍተኛ ቦታ የተቀመጡት የቀ. ኃ. ሥ ቲያትር ሙዚቀኞች አለመጠን አድምቀው ሙዚቃ ያሰማሉ። እነሱም እንኳ እየጨፋፈሩ መላ ቅጥ ጠፍቷቸዋል፤ እኔ በደረስኩበት ጊዜ በመሐሉ ሜዳ ላይ ደናሾቹ ቻቻ ይደንሱ ነበር፤ በዚያ ትልቅ አዳራሽ ብዙዎቹ ወንዶች ትከሻ ላይ ተጋድመዋል፤ ከወንዶችም ሴቶችን ተደግፈው የፈዘዙ አሉ።

በዚያች ምሽት በዚያ አዳራሽ ስለ ፖለቲክ፤ ስለ ድህነት ስለ አስተዳደር፤ ወይም ስለ ግብርና ወይም ደግሞ ስለ ነጋዴዎች ወይም ስለ ሊስትሮዎች ማስቸገር አይወራም። በጠቅላላው የጠቅላላው ተጋባዥ ወሬ «ፍቅር» ብቻ ነበር፤ ለድንገተኛ ደራሽ ክርስቶስ «እርስ በራሳችሁ ተዋደዱ» ያለውን ቃል የፈጸሙ መናንያን የሰፈሩበት ገዳም ይመስላል።

ለጥቂት ጊዜ ቆሜ ቦታ ሳማርጥ ይህን ታሪክ ካየሁ በኋላ ዳንሱ ሲያቆምና ደናሾቹ ሥፍራቸውን ሲይዙ ካልተያዘ ባዶ ቦታ የውስኪ ብርጭቆዬን እንደጨበጥሁ ተቀመጥሁ።

እኔ ካለሁበት ሶፋ ራቅ ብሎ ሦስት ሴቶች ካንድ ወንድ ጋር ተቀምጠዋል፤ ፈዘዝኩባት፤ ፍጹም ደስ አለችኝ፤ እሱዋም ብትሆን ዓይኗ ተነቅሎ እስቲበር ድረስ ዓይታኛለች፤ በኋላም እየሠረቀች ታየኝ ነበር።

ፈጽሜ ዓይኔን ከፊትዋ ላይ ሳላነሳ አየኋት፤ በኔና በሷ መተያየት መሐል አንድ የማሪንጌ ዳንስ አልፎ ሌላ ማሪንጌ ተተካ፤ ለሴት ልጆች የሚገባ ክብሯን ሳልነፍጋት እንደንድስ ጠየቅኋት፤ ተነሥታ ተቀምጣበት የነበረው ቀሚሷን ካስተካከለች በኋላ ድነሳችንን ጀመርን፤ የዳንስ አምሮት ያለቀቃቸው ወጠጤዎች ማሪንጌውን ሲውረገረጉበት እኔው ግን እግሬን

ጠብቄ እንዳቀፍኳት መደነስን ጀመርሁ፤ በትንሹ በአዳራሹ ሜዳ እንደንስ የነበርነው አሥር ጥንድ ሳንሆን አንቀርም።

ይርበተበቱ የነበሩት ልቦቻችን ተገናኝተው እንዳይጨባበጡ ሽፋፋው አወላካፊ የደረት አጥንት ገደብ ቢሆንም በጕድንና በቆዳ እየተፈታተግን በእግራችን ዳንስ፤ ባፋችን ወሬ ቀጠልን።

«ለምን አየሺኝ»

«አንተስ ለምን አየኸኝ»

«ደስ ስላልሺኝ ነዋ!»

«ታዲያ እከለከላለሁ እንዴ!»

«ይሔ ጉጭማ ምንሽ ነው»

«የቱ? »

«አብሮሽ ያለው»

«የሂሩት ፓርትነር ነዋ!»

«የቷ ነች ሂሩት? »

«ጐኔ የነበረችው»

«አንቺ ከማ ጋር መጣሽ? »

«ከሷ ጋር»

«ያቺኛዋሳ»

«የቷ»

«አብራችሁ ያለችው»

«አቤት ወንዶች - ምን አጠያየቀህ? »

«ለማወቅ ብቻ ነው»

«ጠርተህ ጠይቃት»

«አንቺ አትነግሪኝም»

«ለሷ ጠበቃ አይደለሁም»

«ስምሽ ማነው? »

«የማ? »

«ያንቺ»

«ሉሊት ነው - ያንተሳ? »

«ጌታቸው»

«ኤይ ውሸትህን ነው»

«ያጥፋኝ ጌታቸው ነው»

«ከዚያች ልጅ ጋር ትደንስና ጉሮሮህን ነው የማንቀው»

«ከየቷ? »

«አሁን ከጠየቅሀት ጋር»

«ለምን»

«እንጃልህ»

«ምናለበት»

«አላቅልህም»

ሙዚቃው አለቀና በየቦታችን ሔድን፤ ደናሹ ተዳክሞ ስለ ነበረ ቀጥሎ የተሰማው ሙዚቃ ለስላሳ ሆነ፤ የተለወጠው ሙዚቃው ብቻ ሳይሆን የዳንሱም ደንብ ነበር፤ የሴቶች ምርጫ እንዲጀመር ተለፈፈ፤ ወንዱ ሁሉ በያለበት መቁነጥነት፥ ማነቆውን ማስተካከል ሴቶቹን ለመሳብ ያህል ጣርያ ጣርያውን ማየት ጀመረ።

ውሸት ምን ያደርጋል እኔም ብሆን ደንግጫለሁ፤ መራጩ ማንኛይቱ አፎዶ ትሆን ይሆን እያልኩ አስቤአለሁ፤ ባንድ በኩልም እስከ ጭራሹ ባልመረጥ እንደምናደድ አስቤአለሁ፤ ግና የሴቶቹን ምርጫ መብት የፈቀደው ገና ተናግሮ ሳይጨርስ ሉሊት አይታኝ ሳቅ ብላልኝ ነበርና በተስፋዋ ኮቻለሁ።

ልክ ነው፤ አልተሳሳትኩም፤ ባጠገቤ ካሉ አራት ጐረምሶች መሐል ሉሊት እኔ እንዳዳንሳት ጠየቀችኝ፤ ተነሣሁ መሐል ገብተን እንደ ተለመደው በእግራችን ዳንስ በአፋችን የቁም ነገር ወሬ ጀመርን።

«ስኩዊዝ ሚ አር ዩ ባችለር»

«ዋት አባውት ዩ»

«ነኝ»

«እኔም ነኝ»

«አዬ? »

«ሙት»

«ለምን አታገቢም»

«ምን እባክህ የሚረባ ወንድ አይገኝም»

«የምትረቡት እኮ ስታገቡ ነው»

«ኖ አይሚን አባውት - አባውት - አየህ ጠባዩ ጥሩ የሆነ ወንድ የለም»

«ብታገኚስ? »

«አይገኝም እንጂ»

«ታገኛለሽ አልኩሽ»

«ታገኘሁማ አገባዋለሁ»

«ምን ዓይነት ወንድ ትፈልጊያለሽ? »

«ሐንድሰም»

«ፎር ኤግዛምፕል - እኔን ስንት ጊዜ የሚያህል»

«ጀስት አዝዩ»

«አራይት እንግዲያውማ አለሁ»

«ዋት አባውት ዩን ካራክተር»

«ዩ ሲ ዋት ካን አይ ሴይ አባውት ማይ ካራክተር»

«አየህ ዋናው ነገር ዱ ዩ ላቭ ሚ»

«የስ - በጣም እንጂ ሉሊት»

«አራይት ዩ ካን አስክ ማይ ፋዘር»

«ሁ ኢዝ ዩር ፋዘር»«

«አባ ኃይለየስ ናቸው»

«አንቺ ፈቅደሺኝ የለ»

«በደንብ ነዋ»

«እንግዲያውስ ለመጀመሪያ ጊዜ በከንፈር እንፈራረም? »

«እንዴት? »

«የከንፈሬ አሻረ ከንፈርሽ ላይ፤ የከንፈርሽ አሻራ ከንፈሬ ላይ እንዲገኝ እናድርጋ»

«ኡ - ሰው ያየናል»

«በዚህ መብራት እንዴት ይታያል»

«ኧረ ባክዎት ይታያል - ኧረ ባክህ ተው - ኡ አዩን»

//=//

ሚስት ካለህ ሰዎች መሐል እኔ፤ ክፍሌ ፤ ገበየሁ ተሾመ፤ አበበ ሆነን ከወንደላጤዎች ደግሞ ገብረ ማርያም፤ ግርማ፤ ሽንካፋው ዓለሙ፤ ኩሩሩዋ አበራ ሆነው ባንድ ቡና ቤት ስንጫወት በጨዋታው ጉዞአችንን ከሚስት ወግ ላይ ደረስን።

እኛ ባለ ሚስቶቹ ወንደላጤዎቹን ለምን ሚስት አታገቡም ብንላቸው ሽንኬው ዓለሙ «ታማኝና ጥሩ ሴት አትገኝም» አለን። ገብሬም «አዎ» አለ ካገባሁ ስድስት ወር ሆኖኛልና ስለ ሚስቶች ላስረዳ «እርግጥ በሚስት በኩል መልካማቱን ለማግኘት ችግር ነው፤ መልኳማ ባልባሌ ቦታ ትገኛለች፤ እኔም እንደናንተው እንዲሁ ስል ከርሜ አሁን እግዚአብሔር ድካሜን ቆጥሮ ቅድስቷን አጋጥሞኛል» እንዳልኩ የምድር አጫዋቹ ኩሩሩው አበራ «ሉሊትን ነው» ቢለኝ «አዋ» አልኩት።

ለማሽሟጠጥ በጐን አስተያየት አይቶኝ ፊቱን ከኔ መለሰና «ሴትን ቅድስት ናት ብለህ አትመካ» አለኝ፤ ከግራና ከቀኝ ያለውን የወንበሩን ብረት መደገፊያ ለብጨ ጐብደድ አልኩና «ሌሎቹን ልትል ትችላለህ፤ ሉሊትን ግን አትንካብኝ» ብዬ በአነጋገሩ መናደዴን በአተናፋፈሴ ገለጽኩለት፤ አበራ በንቀት ዞር ብሎ አየኝና «እሷስ ብትሆን ሴት አይደለችም? » ቢለኝ እንደተልካሻአዎቹ አይደለችማ» አልኩት።

አበራ የቀኝ እጁን እጐኑ ወዳለሁት ወደኔ አራገበና «እባክህ ተወኝ ጃል» አለኝ፤ እኔም ወንበሬን ተደግፌ እግሮቼን አነባበርኩና ኮራ ብዬ «በውነቱ በሉሊት እመካባታለሁ» ብለው ከመቅጽበት ወደኔ ዞሮ በተናደደ አነጋገር እየቸኮለ «ኧረ ባክህ ተወኝና ሌላ እንጫወትበት? » ቢለኝ እንደሱ ሳልናደድ በረድ አልኩና ሲጃራው መኮስተሪያው ላይ ያሉትን አመዶች በክብሪት እንጨት እየጫጫርኩ «አንተኮ ነህ ሉሊትን እንደ ሌሎቹ ሴቶች ቆጥረህ ያናደድከኝ» ብለው «ልክ ነው» አለና ቱግ አለ።

«ተሳስተሃል» አልኩት፤

«አትቀየመኝም? » ብሎ ጠየቀኝ፤

«አልቀየምህም» ብለው።

«እንግዲያውስ ካንድ ሆቴል ተቀመጥና ሉሊትን ልወዳጃት ይዣት እመጣለሁ» አለኝ።

«አንተ!? »

«አዎ እኔ»

«አንተ? »

«አዎ እኔ»

«አንተ እኮ አጭር ነህ»

«ብሆንሳ»

«የእኔን ሽንጥ የለመደች ሉሊት ትንቅሃለቻ»

«ፈጽሞ አንተ ብቻ አትቀየመኝ እንጂ አሳይሃለሁ»

«እምቢ ብትልህ ምን ትከፍለኛለህ? »

«የወር ደሞዜን ፩፻፯ ብር እለቃለሁ»

«በቃ እሺ»

«አንተስ ምን ትከፍላለህ? »

«እኔማ ሚስቴን ስሰጥህ ምን ልከፈል»

«እሺ አሳይሃለሁ»

በዚህ ተስማማንና ተለያየን፤ ልክ በስምንተኛው ቀን እሑድ ለታ ከአበራ ጋር ተገናኘንና «ታዲያስ» ብለው «እንግዲህ አንተ ለስምንት ቀን ታዝዤ መሔዴ ነው ብለህ ከአዲስ አበባ የወጣህ ምሰል» አለኝ። «ለዚህ አትቸገር ማዘዣውን ነው የማሳያት» ብዬው ተለያየን።

ከመሥሪያ ቤቴ ለስምንት ቀን ወደ ጠቅላይ ግዛት ሒጄ እንድሠራ የታዘዝኩበትን ማዘዣ አስመስዬ አወጣሁ፤ ማታውኑ ለሉሊት መሔዴ ነው ብዬ ማዘዣውን አሳየኋት፤ አዘነች፤ ተከዘች፤ «እስክትመጣ እንዴት

እሆናለሁ? » አለች አፅናናኋት፤ አበራትቼአትና ከቤት እንዳትወጣ አደራ ብዬአት ተሰናበትኳት።

ደብረ ዘይት ሆቴል ከፎቅ ላይ ሆኜ በመስኮት ስመለከት በሩቅ የአበራ ታኑስ መኪና ስትመጣ አየኋትና ከተቃጠርንበት ክፍል ገብቼ ከቁም ሳጥኑ ውስጥ ቆሜ በላዬ ላይ ዘጋሁበት፤ አበራ እንደገባ ቁም ሣጥኑን ቆለፈብኝ።

«ግቢ የኔ ዓለም ሲል ተሰማኝ፤ ከብብቴ የመነጬት ላቦች ጣቴን ወንዝ አርገው ወረዱ ምን እንድትጠጣ ቢጠይቃት «ኦራንጅ ጁስ» አለችው፤ ቦዩ መጠጡን አምጥቶላቸው ሲወጣ አበራ በሩን ቆለፈው ከዚያ በኋላ ቁም ሣጥኑ አጠገብ ካለው አልጋ ላይ ተቀምጠው ወሬ ጀመሩ።

«ባልሽ የት ነው የሔደው? »

«ጐጃም»

«ለምን»

«ለሥራ»

«ትወጂዋለሽ» ደንገጥሁ

«በደንብ ነዋ» - አንጀቴ ቡጥ ቡጭ አለ።

«እኔንስ» - መልሼ ደንገጥሁ

«አንተንም እወድሃለሁ» - ከፉኛ ተናደድሁ

«ከኔና ከሱ ማን ታስበልጫለሽ? »

«እሱንማ እንደባልነቱ አንተንም ወድሃለሁ»

«ጌታቸው እኮ ጓደኛዬ ነው»

«አዬ»

«ሙች»

«ታዲያ ለምን ከዳኸው? »

«አንቺ ለምን እሺ አልሺኝ»

«አንተ ለምን ለመንከኝ»

«ወንድ ስለሆንኩ አማርሺኝ»

«ታዲያ አሁን ይቅርብና»

«ምኑ»

«የመጣንበቱ» - አንቀጠቀጠኝ፤ እንደ ላም አርጂ ብበላት ወደድሁ፤

«አዬ ይሔማ ነውር ነው፤ ብቻ በፊት እናውራ እንጠጣ»

«ለመሆኑ የት ነው ያየሽኝ»

«ምነው አንድ ቀን ጌታቸው አላስተዋወቀንም»

«አዎ አዎ እውነት ነው ልጅዬ»

«ያን ለታ አልጣልኩሽም»

«ወይድ እኔ ልጅት? - አንተ ነህ እንጂ እንዲያው ዓይነህን አፍጠህ ያየኸኝ»

«ምነው አንቺስ ብትሆኝ»

«ኧረ ወይድ»

«አትዋሺ ደስ ብዬሻለሁ»

«ደስ ማለትማ ብለኸኛል» - ይህን ስሰማ ሚስቴን ወንድ ፊት ላላቀርብ ማልሁ።

«ጌታቸው ሲመታ ትከለክይኛለሽ? »

«ምን? »

«ምንም»

እንደጊዜው አመቻቸት እያየን ነዋ»

«ጌታቸው ቅንዝረኛ ነው ወይስ ጨዋ? » - እሳጥኔ ውስጥ እንደሆንኩ በሆዴ ትሩ ጥያቄ ነው አልኩ።

«ብቻ አየህ ወንዶች አይታመኑም እንጂ እንደሚምልልኝና እንደሚለኝ ጌቱ ጨዋ ነው»

«አንቺሳ»

«እኔም ጨዋ ነኝ»

«የዛሬውስ? »

«ከድምር አይገባም»

«ለምን»

«ኢት ኢዝ ፎር ዋን ዴይ»

«ዱ ዩ ብሊቭ ጌታቸው አዝ ዱ አዝ ዩ ዱ? »

«የስ አይ ብሊቭ»

«አትፈቺውም? »

«ኋይ»

«ቢኮዝ አይ ዎንት ቱ ሜሪዩ»

«ኖ ዚስ ኢዝ ኖት ፖሲብል»

«ኋይ»

«የጌታቸው ባልነት ጥሩ ነው»

«እኔ መጥፎ ነኝ? »

«አልወጣኝም፤ - ብቻ አየህ መፍታት ነውር ነው»

«ወድሻለሁ፤ ታዲያ እንዴት ፍቅራችንን እንጨርሳለን? »

«እንዲያልቅ አልፈልግም»

«እንግዲያሳ»

«እያለሳለስን እናዘግምበታለን»

«እንዴት? »

«ጊዜ አለን»

ራሴ ዞረ ተበጠበጥሁ፤ የመኖር ሕይወቴ ተሳተኝ፤ የቁም ሳጥኑን መዝጊያ በኃይል ገፋሁት ልከፍተው ግን አልቻልኩም፤ የመሯሯጥ ሁካታ ተሰማኝ፤ በዚያው በሣጥኔ ውስጥ እንደሆንኩ አለመጠን በሚወርደኝ ላብ እየታጠብሁ የሚያየኝ ላይኖር ዓይኔን አፍጥጬ «ሉሊት እኔ ጌታቸው ነኝ!! ብምርሽ እግዚአብሔር ነፍሴን አይማራት!!» እያልኩ ጮኩኝ።

ካንድ ሩብ ሰዓት የቁም ሣጥን ውስጥ ርብትብቴ በኋላ አበራ የቁም ሣጥኑን ቁልፍ ከፍቶልኝ እንደ እብል ዘልዬ ወጣሁ፤ በዓይኔ ሉሊትን አጥቼ አበራን አንቄ እገላለሁ ስል እነ ገብረ ማርያም፤ እነ ገበየሁ እነ ዓለምሙ እነ ተሾመ ጠፍረው «ዝም በል - እንዲህ መሆንህን ስታወቅ ዱሮውኑ ለምን ፈቀድክለት? » እያሉ በምክርም በተግሣጽም አበረዱኝ፤ «እስዋን አሳዩኝ» ብላቸው ከለከሉኝ፤ መብረድ አይቀርምና እንደ ነገሩ በረድ አልሁ፤ እየማልሁ የሉሊትን ዓይን እንዲያሳዩኝ ብለምናቸው ጠፋችብን አሉኝ።

## ምዕራፍ ፬

እርግጥ ነው ሚስት ለማግባት ያደረኩት ድካማ ቀላል አይደለም፤ እኔ ሳገባቸው እነሱ እየፈቱኝ ስላናደዱኝ አሁንም እንደ ገና መልሼ ላላገባ ማልሁ፤ ለጥቂትቅ ጊዜ ያህል ያለ ሚስት በወንደላጤነት ኖርኩ።

ሚስት ምንድን ናት? የሚል ፍልስፍና አደረብኝ፤ አዘውትሬም «ለእግዚአብሔር እግዚአብሔር ይስጠውና ሜዳው ሁሉ ሴት ነው» እል ጀመር።

ለማ ከሀገር ቤት መጣና እኛ ቤት ሠፈር ለእንግድነቱ የአንድ ብር ጠጅ አስገዛሁለትና እራት ከበላን በኋላ እየጠጣን ወሬ ጀመርን፤ በወሬአችንም መሐል ስለ ሚስት ነገር ቢያነሳብኝ ተንገፍግፌ በደሌን አጫወትኩት።

ለማ በደሌን ሁሉ የሚክስ ዳቦ ወሬ አወራልኝ፤ ለማ እንዲህ አለኝ፤ «እናንተ ያዲሳባ ልጆች ቂንቂኑን ታበዛላችሁ፤ ፈረንጅ እንሁን እያላችሁ እንኳን ፈረንጅ ምንም አልሆናችሁ እኛ ድሮ አንዲት ልጅ ለማግኘት ዓመት ሁለት ዓመት ደጅ እንጠና ነበር፤ እናንተ ግን አዲሶቹ ሱልጡኖች እንዳስቀመጣችሁት ዕቃ ወጣ ብላችሁ አንስታችሁ ትመለሳላችሁ፤ እናንተ ወንጋሮች ሴቶቻችሁ መንቃሮች ስለሆናችሁ መንቃራና ወንጋራ አልወሀድ አለ።

«አንዲት ብጫቂ ጨርቅ ካንገታችሁ ካሠራችሁ ካለ እናነተ ሰው ያለ አይመስላችሁ፤ ፈሎ ከሌላት ጨርቃችሁ የኛ ቀጭን አምተብ ትበልጥ ነበር፤ በኛ ጊዜ ሴት ልጅ ተረከዝዋን ካሳየች ማመንዘር አምሮዋት ነው ይባል ነበር፤ አዲሶቻችሁ ተረከዛቸውን አልፈው ባታቸውን ከፍ ብለው ጭናቸውን ምን ምኑ ይቀራል ሁሉም አሳዩዋቸው፤ እናንተም እንደ ጳጉሚት ውሾች የሴት ጭራ ስትከትሉ ዕድሜያችሁን ፈጃችሁ፤ እኛ የገጠሬዎቹ ምን መሆናችሁን ለማውቅ ተቸግረናል» ቢለኝ ፍዝዝ እንዳልኩ «እናንተ ዘንድ ይሔ የለሞይ? » አልኩት።

ለማ የተንዘረፈበትን ጋቢውን አጣፍቶ እየለበሰ «እኛጋ ወዳጄ አንዴ ካገባች መፍታት አታቅ፤ ደጅ መያዝ አታቅ፤ ባይኗ ገበያተኛውን ሁሉ መያዝ አታቅ፤ ግን ግን የናንተ በሽታ ይሔ የያዛችሁን ልክስክስ ጠባይ እንደ ተስቦ እንዳይዘምትብን እንሰጋለን፤» አለኝ።

«ከእናንተጋ ሚስት አገኛለሁ? » ብለ «ሞልቶ» አለኝ።

«እንግዲያስ ፈልግልኝ»

«ምን ዓይነቷን ትፈልጋለህ»

«ቆንጆ»

«የእንትናን ልጅ አለች»

«የማ? »

«የአጐናፍር - በዘርርዋ በሀብቷ፤ በጨዋነቷ የታወቀች ነች፤ የአብዬ ኃይሉ ልጅ እንኳ አገባታልሁ ይል ነበር፤ ሳይተዋትም አይቀር»

«አየህ ጋሼ ለማ - ሰው የያዛትን መውሰድ ነውር ነው፤ እኔም የምናደደው በዚሁ ነው»

«የለም አልያዛትም - ልጁ መሽተኛ ቢጤ ሆኖ በጅም አላሉት»

«እንግዲያውስ ትሁን»

በዚህ ሁኔታ ከጋሼ ለማ ጋር ተነጋግረን ጨረሰን ልጅቷን ለማየት ተያይዘን ሀገር ቤት ሔድን ሞያ ሊያም ነች ጠጉርዋ ደግሞ ሹርባ ተሠርቶ ቅቤ ብቻ ነው፤ ቀሚስዋ የጐፋን ብልኮ ያህላል፤ የተረከዝዋ ስንጥቃት አይጥ ይከታል፤ ደረቷ ላይ ያለው ጭቅቅት በመሰቅሰቂት ቢያነሱት ይነሳል፤ ሰው ስታይ ደግሞ እንደ አውሬ ትበረግጋለች፤ የፈጨችበት ነው መሰለኝ እጅዋ የወፍጮውን መጅ መስሏል፤ ስትሄድ ደግሞ ገርደፍ ገርደፍ ትላለች፤ ደስ ታልም እንጂ ታምራለች።

መቼም ሚስት ፈላጊ ነኝና ትሁን ትሆነኛለች፤ ብዬ ላገባት ጨረስኩና በሁለተኛው እገሬ አገባኋት፤ ወሬ አይደበቅምና ሳላገባት በፊት አክስቷ እመት አይችሉሽም የቀለሟን እግር በእበት እያጀሉ ቆዳውን በማላላት ሞያሌዎችውና ሲደነቁሩላት እንደ ከረሙ ካገባኋት በኋላ ሰማሁ፤ ቅር አላለኝም።

መጀመሪያ በየሱቲው አሳመርኳት በሽራ ጫማም አረጋገጥዋን ዳንኪራ ከመርገጥ አወጣኋት፤ ገረድ ተዋበች መልካም አድርጋ አከላትዋን በፍልውሀ አጥባታለች ከእጸ ገነት የጠጉር መሥሪያ ቤት ወስዳት እንዳራዳዎቹ ልጆቻችን አስተኮሰቻት፤ ገረዴ ተዋበች እንደ እናትዋ ሆና ከሸነቻት እኔም የቀለሟን መቀነት ፈታሁላት።

ቀለሟ ቆነጀት፤ አሉ ለሚባሉት ለአዲስ አበባ ቆንጆዎች ንግሥት ሆነች፤ በልቤም ውስጥ ዙፋንዋን ዘረጋች፤ አሰልጣኟን ተዋበችን ከቤቴ ካልሔደች ብላ ካባረርናት ቆይተናል።

ስድስት ወር አብረን ስንቀመጥ አንድ እቅን ብቻ አናዳኝ አናድጃታለሁ፤ ወዳታለሁ፤ ትወደኛለችም፤ ለሊት ተኝተን እንቅልፍ ከወሰዳት በኋላ አተኩሬ ስመለከታትና በእግዚአብሔር ጥበባዊ ሥራ ስደነቅ ሳላስበው ያሸልበኛል፤ እርስዋም ብትሆን እንደኔው ናት።

ቀለሚ ከአዲስ አበባ ልጆች እንዳታንስ አስተምሬአታለሁ፤ እስዋም ልበ ብሩህ ናትና በጥቂት ጊዜ በእንግሊዝኛ ከከባድ አረፍተ ነገሮች በስተቀር በጥቂቱ መናገር ችላለች፤ በየተማሪ ቤቱና በየጐረቤቶቻችን ካሉት ልጃገረዶች ጋር ጓደኝነት ይዛለች፤ የእነሱን ምክርም እንዳትሰማ አዘውትሬ እየመከርኳት እሺ ትለኛለች፤ እስተናካቴው ሁሉንም እርግፍ አርጋ ከዘውድነሽ ጋር ብቻ ጓድ ሆናለች።

ዘውድነሽ የባላምባራስ ክፍሌ ልጅ ናት፤ ዕድሜዋም ቢሆን ፳፱ ዓመቷ በመሆኑ ነፍስ አውቃለች፤ ዘውድነሽም ባል አላገባም ብላለች እየተባባሉ የምትኖረው ከወላጆችዋ ጋር ነው፤ ዘውድነሽ እንደ ቀለምዬ መቀነቷን ያልፈታችና ገና ልጃገረድ ናት አሉ።

//=//

እሑድ ለታ ደስ አልልህ ብሎኝ ከቤት ተኝቼ ልውል ቆረጥሁ እስከ ፰ ሰዓት ከቀለምዬ ጋር ተኝተን ዋልን፤ ቁርስ ይሁን ምሳ ምድቡ ያልታወቀለትን ምግብ ከበላን በኋላ «እባክህ ከዘውድነሽ ጋር ልሒድ ፍቀድልኝ» አለችኝ።

«ወዴት? » ብላት

«እህቷ እታገኝ ታማለች ስላሉ እኔም ልጠይቃት»

«ትቆያለሻ? »

«አልቆይም ቶሎ እመጣለሁ»

«እሺ»

ቀለሚ ወትሮ ወደ ውጭ ስትወጣ ከምታጌጠው ይበልጥ አጌጠች፤ ሽፋልዋን ተኳለችው፤ ባትዋን በቅባት ባሸሸችው ጊዜ ሆዴን ነደድ አለኝ፤ «ማዳለጥዋ ማንን ለመጣል ይሆን» አልኩ፤ ሔደች።

ልክ ፲፪ ሰዓት ተኩል ሲሆን ተመለሰች፤ ከእልፍኝ ሆኜ መጽሐፍ አነብ ነበርና የቤታችንን በር ስትገባ «እህህ» «ምን ሆንሽ? » ብዬ ብጠይቃት «ምን ሆንኩ» ብላ ጠየቀች።

ተከዛ ተቀመጠች፤ «እታገኝ ደህናም አይደለች? » ብላት «ምን ትሆናለች? » ብላ ጠየቀችኝ፤ «ዘውድነሽ አስቀየመችሽ እንዴ? » ብዬ ብጠይቃት «ምን አረኩና» ብላ መልሳ ጠየቀችኝ፤ የዋለችበትን ጉዳይ ስጠይቃት ያልዋልኩበትን ስለምትጠይቀኝ መልስ እያጠረኝ ተውኳት።

ሳንነጋገር አመሸን፤ ሳናወራ እራት በላን፤ ሳንጫወት ተኛን፤ ሳልቆጣት፤ አኮረፈችኝ፤ ሳላስቀይማት፤ ጠላችኝ፤ ሳከብራት ናቀችኝ፤ ተኛን ለወትሮው ታቅፈኝ የነበረችው ፊትዋን ዞራ ተኛች፤ «ምነው» ብላት «ምኑ» አለችኝ።

«ለምን ዞረሽ ተኛሽ? »

«አሞኛል»

«ምንሽን? »

«ሁለመናዬን»

«ዱሮ ሲያምሽ ደረቴ ላይ አልነበር የምትተኚው? »

«ዛሬ ደሞ እንዲህ አሰኘኝ»

«ለምን»

«እንዲሁ»

«ዛሬ ምን ነካሽ? »

«አላቅልህም ትተኛ እንደሁ ተኛ አለዛ አልጋውን ትቼልህ እሔዳለሁ» አለችኝ፤ ተውኳት፤ ሌላ መውደድዋን አወቅሁባት፤ ከዋለችበት እንደቀናት ገባኝ ነደደኝ አንገበገበኝ ልማታም ከጀልሁ ሰው ናት ብዬ ያገባኋትን ሚስቴን አህያ አድርጌ አልደበድባትም ብዬ ተውኳት።

ነጋ፤ ማለዳ ተነሳች በሦስት ሰዓት ተነሳሁ፤ የለችም፤ ገረዴን ወለቱን የት እንደሔደች ብጠይቃት «ቤተ ክሲያን ብለው ሔዱ» አለችኝ ወደ ሥራዬ ሔድሁ በሰዓት ስገባም አልተመለሰችም፤ ጦም ቀን ነበርና ልታስቀድስ ቆይታ ይሆናል ብዬ ምሳዬን በልቼ ወደ ሥራዬ ሔድሁ።

ማታም ሳትመጣ ቀረች በነገታውም ውላ አደረች፤ ጠግባ እንደ ሔደች ጠግባ ትመለስ ይሆናል ስልቀረች፤ ቀረች።

የምወዳት ሚስቴ ቀለሚ፤ ከቤተ ክርስቲያን ስብከት ሰምታ ትመንን - ከበረሃ ትግባ - ወይም እንደ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ታርግ - ወይም እንደናዳብና አቢሁም ከሰማይ የወረደ እሳት ይብላት - ወይም ደግሞ እንደ ቆሪና እንደ ዳታን መሬቲቱ ተከፍታ ትዋጣት - ወይም እንደ ሮብዓም እጅ ተገትራ ትቅር - ወይም ደግሞ ንጉሥ ሰሎሞን ልቡ ጥፍት ብሎላት «.......አንቺ ሙሽራ ከኔ ጋር ነይ እቴ ሙሽራዬ ልቤን ማረከሺው፤ ፍቅርሽ ከወይን ይበልጣል፤ ሽታሽ ከሽቱ ሁሉ ይበልጣል፤ ከንፈርሽ የማር ወለላ ያንጠባጥባል፤ የተቆለፈ ገነት፥ የተዘጋ አትክልት የታተመ ምንጭ ነሺ.......የሚላት አክናፊ አጋጥሟትም እንደሁ እንጃላት ጠፋችብኝ።

## ምዕራፍ ፳

ፊታውራሪ ገበየሁ የእናቴ ታላቅ ወንድም ናቸው፤ እኔን አፈር ይብላኝና ፊታውራሪ ገበየሁ እንደ ዛሬ ጥርኝ አፈር ሳይሆኑ የዚያን ጊዜ የ፷፪ ዓመት አዛውንት ነበሩ፤ በምን አነሳኸኝ አይበሉኝና ፊታውራሪ ገበየሁ በኛ በዘመዶቻቸው መሐል ብቻ ሳይሆን በሠፈራችንም በሌላም ቦታ የተከበሩና የተፈሩ ሰው ነበሩ።

የዛሬ አያርገውና የፊታውራሪ ገበየሁ ፊታውራሪነት የጫካ ነበር፤ በፋሽስት ዘመን የመትረየሱ ቃታ ግሎ እጃቸው እስቲመላለጥ የተኰሱ ለታ ከባላምባራስነት ፊታውራሪ ተባሉ አሉ።

ፊታውራሪ ገበየሁ ብዙዎቹን አጋብተው ዛሬ ሁሉም ወልደው ከብረው ተዋደው ይኖራሉ፤ የአክስታችን ልጅ ሙሉ እመቤት ጠላ ትሸጥ አግኝትወአት ለክብር ዘበኛው ተራ ወታደር ለዋቅቶላ ድረዋት ዛሬ ፫

ወልዳለት በሀብቱም በኩል እንደ ስሟ ሆናለች፤ ዋቅቶላም ሻምበል ሆንዋ፤ በጠቅላላው ፊታውራሪ ያጋቧቸው ባልና ሚስቶች ከመውለድና ከመክበር በስተቀር መፋታት የሚባለውን ነገር እንደማያውቁ እኔም እራሴ አውቃለሁ።

ፊታውራሪ ስለኔ ሚስቶች ሁልጊዜ ይበሳጫሉ፤ «ለኔ አጋቢነት ፋንታ ስጠኝ» እያሉኝም በጅ ሳልላቸው ከርሜአለሁ፤ በዚሁ ምክንያት ፊታውራሪ «እንደፈለጋቸው ይጨማለቁበት» ብለው ተወት አድርገውኛል፤ ፊታውራሪ በማጋባቱ በኩል ይተውኝ እንጂ የእኅታቸው ልጅ በመሆኔና አንዳንዴም እቤታቸው እየሔድሁ ሳጫውትቸው ስለምውል ይወዱኛል።

አዳነች ምጥ ይዟት ሁላንም ተጠርተን ከቤትዋ አምሽተን ነበር፤ ፊታውራሪ ለጥቅምት ብርድ ካፖርታቸውን ለብሰው ጠጉር የሌለበት መላጣ ራሳቸውን በሻርፕ አስረው ከሣሎን ተቀምጠን ስንጫወት ዕልል ተባለ፤ እናቴም ከጓዳ መጡና «ባምላካችሁ ሴት ወለደች!» አሉ፤ ብዙዎቹ ደስ አላቸው፤ እኔ ግን ያደጉት ሲያስቸግሩ ሌላ አስቸጋሪ ደግሞ በመወለዷ ከፋኝ።

እማዬ አበበችን ገንፎ አሲዘው መጡና ከኛ ጋር ሆነው ስንበላ አንድ ጉርሻ ገንፎ ከቅቤው ነክረው ጐረስ አደረጉና «ፊታውራሪ? ምነው የጌታቸውን ነገር ቸል አልከው? » ቢሏቸው፤ ፊታውራሪ እገንፎው ላይ እንዳጐበደዱ ገንፎ ገንፎውን እያዩ «የምኑን? » አሏቸው። እማዬ እንደ ተከዙ በገንፎው ላይ አቀርቅረው የሚጐርሷትን እያስተካከሉ ለዘብ ባለ አነጋገር «ምነው ብትድረው? » ቢሏቸው፤ ፊታውራሪ ወደ ኋላቸው ደገፍ አሉና የጐረሱትን እያጣጣሙ «እምቢ አለኛ» አሏቸው።

«ኧረ እምቢ አይልህም ፊታውራሪ»

«ብሎኛል እንጂ - እኔንም አታምኚ»

«ኧረ አይወጣውም»

«ጠይቂው»

«ይሁን በጄ - ያለፈው ይቅርና በል አሁን ዳረው» ቢሏቸው ፊታውራሪ በእጃቸው የያዙትን ገንፎ እንደያዙ ቅቤውን እያንጠባጠቡ «እሱ እኔው ተነጋግሬ ልጨርስ ይላል» አሉና ጐረሱ፤ እማዬ አጠገባቸው ከነበረው ሰሃን ውስጥ ቅቤ በጭልፋ ጨልፈው ወደ ገንፎው ጨመሩና እያስተካከሉ «አይልም» አሏቸውና ጭልፋውን ከሰሃኑ ውስጥ አስቀመጡት።

ፊታውራሪ እንደ ገና አጐብድደው ከገንፎው ቆርሰው እያንከባከቡ «ልጅሽ ነው የማይፈልገው ራሱን የቻለ ነው» ብለው አንጋጠጡና የያዙትን ገንፎ አፋቸው ውስት አስቀመጡት፤ እማዬ ልብሳቸውን ቅቤ እንዳያበላሸው እጆቻቸውን አንዘርፈው አጣምረው ተቀመጡና አንገታቸውን ቀለስ እንዳደረጉ ወደ ፊታውራሪ እያዩ «እንዲህ አትበል ወንድሜ - እሱ ልጅ ነው፤ አባት ይለው አባቱም፤ አጐቱም አንተው ነህ የሱን ነገር ሳትዘክር አሁን በል አጋባው» አሏቸው።

ፊታውራሪ እናቴን ገርምመው «በጅም አይል ስልሽ» ቢሏቸው እማዬ አንገታቸውን ዘንበል አድርገው አቀረቀሩና በኃዘን «ኧረ ይላል ፊታውራሪ» ቢሏቸው ፊታውራሪ ከነወገባቸው ወደኔ ዞር አሉና በኮራ አስተያየት እያዩኝ «ጌታቸው ልዳርህ? » ቢሉኝ ፎቶዎቹ ጠበውን የተቀመጥኩት ቀዩዋ ቡፌት ላይ ነበርና ገንፎ የበላሁበትን እጄን እየጠራረግሁ ፈገግ ብዬ «ምን ከፋኝ» አልኳቸው።

«ምን ዓይነቷን ነው የምትፈልገው? »

«ቆንጆ»

«ቆንጆ አትውደድ»

«ለምን»

«አንተ እንደትወዳት የሚወዳት ይበዛል፤ የሚወዳትም ሲበዛ ጠላትህ እየበዛ ይሔዳል»

«ኋላስ»

«ጐመድ ያለችው የኔ ቢጤ ትሻልሃለች»

«ይሁና»

«በሀብትሳ እንዴት ነው ሐሳብህ»

«ከያይነቱ አግብቼ አልበረከቱልኝም፤ ቢሆንም ጌታ ትሻላለች»

«ጥሩ ነው» አሉኝ ፊታውራሪ «አየህ ጌታቸው እንዳተ ባላውቅ እንደኔ መናጢ ደሀን ማግባት ዝርያዎችዋን መርዳቱ ሥርህን ይነቅላል፤ የድሀ ልጅ ጥጋብም አይቻልም፤ የሀብታም ልጅ ማግባትም ቂሎች አባቶች ባሎችን እንደ አሽከሮቻቸው ይቆጥራሉ፤ ልጅቷም ትንቀባረርብሃለች፤ ያባትዋን ቤት ዘበናይነት ካንተ ትፈልግብሃለች፤ የሀብታም ዘመድ ብዙ ነውና ዘመንድ መጠየቁም ሥራ ያስፈታሃል፤ ለጠበልም ሆነ ለጠዲቅ ትንሽ አይበቃህም፤ ሌላው ይቅርና ከሚያልቀው አዝማድ ብዛት የተነሣ ዘፈን የምትሰማበት ጊዜ እንኳ አታገኝም፤ ለድሆች እንደሚመስላቸው ሳይሆን የሀብታሞች ኑሮ በሕሊና በኩል ሲኦል ነው፤ ወህኒ ነው፤ ዘብጥያ ነው፤ ከርቸሌ ነው፤ ላግባ ካልክ የባሻ አጥናፉ ልጅ አለችልህ፤ አባቷም ምራቁን የዋጠ ነው፤ ጥርሱን ነክሶ ልጁን እስከ ስምንተኛ ክፍል አስተምሯታል፤ እናቷም ብትሆን ደኅና አድርጋ የቤት ሞያ አስተምራታለች፤ የልጅነቱን ጨዋነት ዓለም መስክሮላታል። ሠፈር በሙሉ መለኩሲቱ ነው አሉ የሚሏት ታገባ እንደሆነ ልነጋገርልህ» አሉኝና ነገራቸውን በዚህ አቆሙት።

ደስ አለኝና ፈገግ ብዬ «ማን ትባለለች? » ብላቸው ፊታውራሪ የጭናቸውን ጉያ ማከክ ስለሚወዱ እንደ ተለመደው እያከኩ «እታገኝ ይሏታል፤ እንዲያውም ብዙ ሰው በቁልምጫ እታቱ ነው የሚሏት» አሉኝ።

//=//

እንደ ዕድል ብሎልኝ ሥራዬ ሁልጊዜ ወደ ውጭ ያስወጣኛል፤ አንድ ጊዜ ባንድ ሥራ ታዝዤ ወደ ፈረንጅ ሀገር ሔድሁ ስሔድም ሚስቴ እታገኝ በምንም ሁኔታ እንዳትቸገርና እንዳታዝን፤ እንዳትበሳጭም በማለት ሁሉን ነገር አሟልቼላት ሔድሁ።

ከመሔዴ በፊት መሰንበቻችንን ስለ መለያየታችን ተጨንቀን ስንወያይ ስናዝን ከረምን፤ በመጨረሻይቱ ዕለት ያ - የሰማይ መርከብ ያ - ጀፌ አሞራ ጥንቦቹ አርጎ ሊጐርሰን ወደ ሚያርፍበት ሜዳ ከእታገኝ ጋር አብረን ሔድን፤ በዚያም ጊዜው ደርሶ ተጐርሰን እስትንበር እኔና እታቱ ከተለየ ቦታ ሆነን ያን ሁሉ ሽብርና ትርምስ ከመጤፍ ሳንቆጥረው ስናወራ፤ በእታቱ ጉንጮች ላይ ከእታቱ ዓይኖች የሚፈሱት የሐምሌ ውሀዎች ደረቷን እየገመሱ ሲያልፉ እኔንም ቢሆን እንደ መስከረም ዝናም ዧ መንዧ ያደርጉኝ ነበር።

የዚያን ለታዋም የአዲስ አበባዋ ፀሐይ ከድሬ ዳዋ ጨረቃ እኩል የማትሞቅ ስለ ነበረች ብርድ፤ ፍቅር፤ ዕንባ፤ የመለያየት ትውስታ ተደራርበውን ነበር።

እታቱን የሚያስበረግጋት ስሜ፤ የምኮራበት ስሜ፤ በሬዲዮ ተጠርቶ ቦታህን ያዝ ስባል እንጀቴን ቡጭቡጭታ ኮቴን እየገፈተረው አዝራሮቼን ሊበጥስ ምንም ያህል አልቀረው እታቱም ብትሆን ንፍጥና ዕንባዋ ተቀላቅሎ የለበሰችው የሀገር ልብስ ያ ባዘቶ ፈትል ርሶ እስቲጨመቅ ሳልሞት ለቁመናዬ አለቀሰችልኝ።

የመጨረሻውን መሳም ስስማት የእታቱ፥ ዕንቦች ለመታሰቢያ ያህል በኮቴ ትከሻና በሸሚዜ አንገት ላይ ተርከፍክፈው ቀሩ፤ እታቱ በላዬ ላይ ተጠምጥማ ስታለቅስ ጉዳዩ የሚያገባቸው የእታቱ ጓደኞች እነሰብለ ወንጌል ሁሉ ሊረዷት አለቀሱላት፤ ተሰናበትኳት፤ የእታቱን ፎቶ ግራፍ አቅፋ የያዘችውን መጽሐፌን ጨብጬ በሆዴ እያለቀስሁ ከጀፌው ሆድ ውስጥ ገብቼ ካንጀት ጉበቱ አጠገብ ሥፍራ ያዝሁ።

በጭላንጭል እታቱን ሳያት ዕንባ ያራሰውን መሐረብዋን እያውለበለበችልኝ መልሳ ዕንባዋን አጋሰስ ለሰው ዕንባ ቁብ የሌለው በደዊ በድን አንጠልጥሎኝ አየር ላይ ከነፈ፤ ልቤነታቱ ዘንዳ አስቀምጬ በሳንባዬ ብቻ እየተነፈስሁ እንደ ቅዱስ ሚካኤል ወይም ከሳጥናኤል ጭፍሮች አንዳንዱ ከምድር በላይ ከሰማይ በታች እንደ ቅዱስ ገብርኤል ሰይፍ እያንዣበብሁ በረርሁ፤ ከእታቱ ጋር በሳቅ ተጋብተን በለቅሶ ተለያየን። ተጉዤ ካይሮ እንደደረስሁ በፒራሚድ ፎቶ ግራፍ ጀርባ ላይ

«የፍቅር እመቤቴቱ፤

ደኅና ሁኚ እታቱ፤

የሰማይ አሞራ

ለየኝ ካንቺ ጋራ፤

አሞራው በሮ

አደረሰኝ ካይሮ፤

ሳሚልኝ ከንፈርሽን

የጥርሶች መዝጊያሽን፤

እታቱ ቆንጆዬ

እንዴነሽ እምዬ

ደህና ሁኚ እታቱ

አለፈ ሰዓቱ፤

በደኅና ሰንብቺ

እበረታለሁ በርቺ» የሚል ቃል ጽፌ ፖስታ ቤት አገባሁላት፤ አሁንም ተጉዤ ያን ጨለማ ባሕር እንደ ዮናስ ፈርቼ ከዓሣ ሆድ ሳልሸሽግ ለዓሣዎችና ለባሕር ውስጥ ሠራዊቶች መልአክ ሆኜላቸው ካለፍኩ በኋላ አቴን ስደርስ «በመረረ ጉዞ

ልቤ ተመርዞ

በፍቅር ተይዞ

በናፍቆት ተክዞ፤

ከአቴን ደረስኩ

አንቺን እያሰብኩ፤

ታቱ እወድሻለሁ

እናፍቅሻለሁ፤

አለቅስልሻለሁ፤

ደህና ሁኚ

እስትንገናኝ» የሚሉ ቃላት የአቴን አካደሚ ሥዕል ባለበት ጀርባ ላይ ጽፌ በፖስት ቤት ላኩላት፤ ከምሔድበት ሀገር ደርሼ ያንድ ሦስት ወር እንግዳ እንደሆንኩ ከአዲስ አበባ በየጊዜው ከሚያደርሱኝ ፖስታዎች መሐል ከሳሙኤል ዘንድ አንድ አሳዛኝ ደብዳቤ ዓርብ ዕለት ደረሰኝ፤ አነበብኩት፤ አዘንኩ፤ ሴትን የፈጠረን እግዚአብሔርን አማሁት፤ ምድር ምድር በዳ ሆና እንዳትቀር ብሎ በመፍጠሩም መልሼ ስቡሕ ተሰብሐ አልኩት።

በደብዳቤው የሰማሁትን ነገር ለእታገኘሁ ጻኩላት፤ በደብዳቢዬም ላይ አለፍ አለፍ እያልኩ እንዲህ አልኳት.......እታቱ አዘንኩብሽ፤ እኔ ያንቺን የቅድስቲቱን ጭን አደረሺው አሉ፤.......እታቱ? ምነው ሌሎቹን በሆነ? እወድሻለሁና ያሉኝን አልደበቅሽም፤ ዘውዴ ኦፔሉን ለቀልሽ ዝነጣ ይዘሻል አሉ፤ በሞንዳላ አቃብጢዎች ሳለውጥሽ ለወረት ሸጥሺኝ እታቱ፤ አዘንኩብሽ፤.......እታቱ በመኝታዬ ላይ ሌሎችን አስተኛሽበት? ጠረኔ ይፋረድሽ ክንዴ ይጣልሽ.......አናደሽኛል ብዬ ዛሬ እንደነበርንበት ጊዜ እታቱ እልሻለሁ ግን እታቱዬ ለወጥሺኝ......

በፖስታ ቤት ወዲያውኑ ላኩላት፤ ለካሉላት ፲፰ ቀናት ያህል ቆይቶ በደረሱኝ ፖስታዎች መሐል የእታቱን ጽሑፍ አውቄው ከሌሎቹ መርጩ በቀደምት አንቬሎፑን ቀድጄ አነበብኩት፤ አልፎ አልፎም «......ጌቱ አትስማ......በኔና ባንተ ፍቅር ቀንተው ሊያጣሉን የሚሞክሩ ሰይጣኖች ናቸው፤......ቢሉህ ቢሉህስ እንዴት ከዘውዴ ጠረጠርከኝ?.......ያን ለታ ተኝጠን ምን ተነጋገርን?......እመነኝ ባታምነኝም የልቤን የሚያውቅልኝ ኢየሱስ ስለሆነ በምንም ነገር ሳላፍር እኖራለሁ፤ አንተ ግን የሰው ነገር በመስማትህ አፈርኩብህ፤ ቀንና ሌት በናፍቆትህ ከማልቀስ በስተቀር ምን ጊዜ ደልቶኝ ነው ከሌላ ጋር የምዳራው?.......እኔ ለራሴ ወንዱም ወንድ አይመስለኝም፤ በአዲስ አበባ አንድ ነበርክ፤ አንተው ሔድክ፤ .......በሃይማኖቴና በእምነቴ ጸንቼ እጠብቅሃለሁ.......» የሚሉ ቃላት አሉበት።

የተወሰነልኝን ጊዜ ጨርሼ ወደምወዳት ሚስቴ ወደ ናፈቀችኝ ሀገሬ ተመለስኩ፤ እንኳን ሚስቴ እታገኘሁና ጥላሸት ቆዳ ያላቸው የምጣድ ጀርባ መሳዮቹም ናፍቀውኛል፤ ለሁሉም ደረስኩ፤ በሰላም ተቀብላኝ በዓለም በደስታ አብረን ከረምን።

አንድ ቀን ወደ ስራዬ ሔጄ እንዳጋጣሚ በድንገት ከቤት ብመለስ ከቤት አንድ መልከ መልካም ዛውላና ቁመቱ የሚያምር ሎጋ ክብር ዝበኛ ተቀምጦ ከእታገኘው ጋር ሲያወራ አገኘሁት፤ ወዲያውኑ እንደገባሁ እታቱ «ከወንድሜ ከመለስ ጋር ተዋወቁ» ብላ አስተዋወቀችኝ፤ ከዚያም በፊት ለምን እንዳላስተዋወቀችኝ ብጠይቃት «በሥራ ምክንያት ወደ ውጪ ሔዶ ነበር» ብላ መለሰችልኝ፤ እሱም «አዎ፤ ወደ አሜሪካ ለትምህርት ሔጄ ነበር» ብሎ አረጋገጠ።

ከመለስ ጋር ወዳጅ ሆንን፤ ራቱንም ሆነ ምሳውን ከኛው ቤት ይበላ ጀመር፤ እኔ ቀድሜ ከሥራ ወደ ቤት በምገባበት ጊዜ «መሰለ ሳይመጣ» እያለች ምሳችንን ሳንበላ እንጠብቀዋለን፤ መሰለንም እታቱ እንደ እናቷ ልጅ አዘውትራ ትጋብዘዋለች፤ እኔመ አይደንቀኝም።

አንድ ቀን ጓደኞቼ መሰለ የእታገኘሁ ውሽማ መሆኑን ነገሩኝ፤ አለመሆኑን በብዙ መንገድ ብከራከራቸው መሆኑን በብዙ ጐዳና አስረዱኝ፤ እኔም እንዲህ ዓይነቱን ዕድል የሰጠኝን አምላክ አማረርኩት፤ ሴቶቹ ብቻ ሳይሆኑ ወንዶቹም ጭምር ረክሰው በማርከሳቸው አዘንሁ፤ ሆኖም ከጆሮ ይልቅ ዓይን ይቀርባልና በወሬ ሳልፈታና ሳልፈታት ወደ ጅማ ለመሔድ ተነሳሁ።

ቅዳሜ ለታ ማለዳ አውቶብስ ተሳፍሬ የጅማ ጉዞዬን ቀጠልኩ፤ ከወሊሶ ወርጄ ስጫወት ውዬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስሁ፤ ከምሽቱ በ፫ ሰዓት ወደ ቤቴ ብሔድ መሰለ ከሳሎን ተቀምጦ በጭላንጭል አየሁ፤ ግራ እጁን እታገኝ ትከሻ ላይ አድርጓል ሁለት ፍንጃል ሻይ ከነማቅረቢያው ጀበና ጋር እፊታቸው አለ።

ቅናት ልቤን መታኝ፤ ሕሊናዬን ሰወረው ወዲያውኑ ተጽናናሁ፤ ላይሆንም ይችላል፤ ወንድምም እህቱን ሊያቅፍ ይችላል፤ መረጃው ሌላ ነው ብዬ ወደ ኋላዬ ተመለስሁ፤ ያን የምወደውን ከንፈሯን ሲስማት ካላየሁ

አላምንም አልኩ፤ በስውር ተመልሼ በስውር ቦታ አመሸሁ፤ ልክ ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ሲሆን ወደ ቤቴ እንደገና ተመለስኩ።

መብራቱ ጠፍቷል፤ ጨልሟል፤ ባላየውም አጋንንቶች የሚኖሩበትን ሲኦል መስሏል፤ ቤቴ ቀፈፈኝ ቤቴን ፈራሁት፤ የቤቴ መዝጊያ የሌላ መሰለኝ የደጃፌ አታክልቶች አይተውኝ የታዘቡኝ መስለኝ የዛፎቹ ሽውሽውታ «ዓይተንሃል አንተ አታላይ» የሚለኝ መሰለኝ፤ በደህና መሐል ያለፈችው ጨባሳዋ ጨረቃ «እይቼሃለሁ ጌታቸው፤ ሥራህም ነውር ነው፤ ሚስትህን በከፉ አትፈትናት፤ ብታደርገውም ዝለላት» እያለችኝ መሰለኝ፤ ወደ ኋላዬ ምልስ አልኩ፤ አዘገምኩ ጨክኜ ሔድኩ፤ ከሆቴል ተከራይቼ ተኛሁ።

እንቅልፍ አልወሰድ አለኝ፤ ስድቻ መታኝ፤ እንደ ገና ተነስቼ በድፍረት ወደ ፈራሁት ቤቴ ሔድሁ፤ ደጄን በጄ መታሁት፤ ደበደብኩት፤ የመስኮት ቃቃታ ሰማሁ፤ ዞሬ ስደርስ መሰለ በርሮ አመለጠኝ፤ ብገባ እታገኘን አጣኋት ሔዳለች እንደወጣች ቀረች።

ከብዙ ቀናት በኋላ ተገናኘን፤ ያለፈውን ረስተን ሰላምታ እንሰጣጥ ጀመርን፤ በሰማይ ያሉት የሁለቱም ክፍል መላእክት ይመስክሩብኝ እታገኘሁ እንደ እቴ መስላ ታየችኝ፤ እያደር ይቆጨኝ ጀመር፤ ከብት መሆኔ የላይ ጥርሶቼን አስወልቆ ሳር ሊያስበላኝ በማድረሱ ተጸጸትሁ፤ ጅላጅል እበት ወንድ በመሆኔ አዘንሁ።

የነበርሁበትን ቤት ለቅቄ ከሠራሁት አዲስ ቤት ስገባ ከእታገኘውሁ ዘንድ ሔጄ «እባክሽን የቤቴን ዕቃዎች አሰናጂልኝ» አልኳት እሷም በእህትነቱ ኮርታ ከበቱ መጥታ ዕቃዎቼን ስታዘጋጅ ውላ አመሸች ልሒድ ብትለኝም አብረን እንድናድር አደረኩ ሌሊቱንም እንዳትሞት እንዳትሸር አድርጌ ከገረፍኳትና ጠጉርዋን በደረቁ በሰንጢ ከላጨኋት በኋላ ልክ እኩለ ለሊት ላይ በመኪና ወስጄ እዘመዶችዋ ደጅ ጥያት ተመለስሁ።

በነጋታው ጀግኖችም ዘመዶችዋ ከሥራዬ ቦታ መጥተው ግሥላ እየሆኑ ሁኔታውን ቢጠይቁኝ ሳልናደድ በጥሞና ታሪኩን ዘርዝሬ አጫወትኳቸው። እነሱም መልካም አዛውንቶች በመሆናቸው እንዳመጣጣቸው ሳይሆኑ በርደው «ያለመግደልህም የዛሬ ዘመን ልጅ ሆነህ ነው» ብለውኝ በፍቅር ተለያየን።

«ባንተ ምክንያት ተገረፍኩ» ብትለው የዋሁ ዘውዴ እንደ ልጃገረድ ጋብቻ አስደግድሶ በልጃገረድ ወግ በጉርድ ቧል አገባት፤ እኔም አልቀናሁም፤ ከሦስት ወር በኋላ ሌላ በመያዝዋ ዘውዴም ፈታት።

## ምዕራፍ ፯።

ይሔን ያህልም ቆንጆ ናት ተብላ አይደነቅላትም እንጂ ደማም ነች፤ ወላጆችዋ ግን ውቢቱ ብለዋታል፤ እንያንዳንዶቹ ሴቶች እንኳ በቂዋን ባትማርም የትልልቅ ሰዎች ወገን በመሆንዋ እንደ ድሆች ልጆች ሳትለፋ ከገንዘብ ሚኒስቴር ሥራ ይዛለች።

ደሞዝዋም ቢሆን የማይገባት ሲሆን ለወላጆችዋ ክብር ሲባል የሚገባት ሆና ተገኝታለች፤ ዕድሜዋም ወደ ፴ ዓመቱ ነው።

«ልጃገረድ ነኝ» አለችኝ፤ «የሚያመሽና የሚሰክር ወንድ አልወድም» ትብለትኝ «ይህን መሳይ እጥባይ የለኝም አልኳት፤ «ደግሞ የሚያበሳጨኝና እስከ ዛሬም አላገባም ብዬ የቆየሁት ወንዱ ላያት ሁሉ ሞትኩ ሲል በማየቴ ነው፤ ሚስታቸውን እያስቀመጡ ከሌላ ሴት ሲሔዱ እያየሁ እንደነደደኝ ነው» አለችኝ። ይህን መሳይ ጠባይ እንደሌለብኝና እንደማላደርገው ቃል ገባሁላት።

ምንም እንኳን እኔና በስዋ ነገሩን ብንጨርሰውም ለወጉ ያህል ለከበሬታም ለወላጆችዋ አማላጅ ላክሁ፤ እንደ ሕጉና እንደ ወጉ አማላጆቹ እሑድ ጠዋት ግን ገደማ ሔደው ወደ ሰዓት በኋላው ገደማ ተመለሱ፤ እነሱም ነገሩ እንዳልሆነላቸው አጫወቱኝ፤ ሻለቃ አክሊሉ «ነገሩ አልሆነልህም፤ ስላንተ ያቀረብላቸው ማስተዋወቂያ ሁሉ ካንጀታቸው ጠብ የማይል ሆነ» አለኝ።

ነገሩ እንዴት እንዲህ እንደሆነ ብጠይቀው ባሻ ዱባለ «ምን ያስደባብቃል የሚቆጠር አጥንት የለህም» አሉኝ፤ ብገሸለጥ ጐድኔን ብገፈፍ ሠረሰሬን ለማስቆጠር የምችል መሆኔን ሳውቀው አባቴ የጫካም ሆነ የከተማ ማዕረግ ስላልነበራቸው ከውቢቱ ጋራ ያሰብነውን ጋብቻ ውሾችን ይመስል አጥንት አጣላን።

ይህንኑ የማይጐረደም ወይም የማገሸለጥ ወይም እንደ አኒሳ የማይመጠጥ አጥንት ያመጣውን ጠብ ለውቢቱ ብነግራት ውቢቱ በአጥንት ነገር ከፋት ወላጆቿንም ለኔ ለጌታቸው አማችልኝ፤ ወቀሰቻቸው ከነሱ በመወለደዋም ከፋት፤ እግዜርንም አማረረችው።

«አጥንት ለውሾች እንጂ ለኔው ለውቢቱ አይበጀኝም» አለችኝ፤ «እንግዲህሳ» ብላት «ባለው አጥንት አገባሃለሁ» አለችኝ፤ ስለወላጆችዋ መቀየም፤ ከነሱም ተቀያይሞ ስለሚያዘው ትዳር፤ አባት በወላጅነታቸው ስለሚያመጡት ጉራ ከረዩ፤ የናትዮዋ የባላቸውን መገፋፋት፤ ውቢቱ ከነሱ ተለይታ ለመኖር አለመቻልዋን ሁሉ አስብኩት፤ መረመርኩት፤ አጠናሁት፤ መሰንበቻዬንም አንዳንዴ ብቻ የውቢቱ አሳሳም ቢያስረሳኝም ነገሩን ሳወጣና ሳወርድ፤ ስጥልና ሳነሣ ከረምሁ።

እርግጥ ውቢቱ እንደምትለኝ ባደርገው ጊዜ ያነሣቸው አባትዋ ከጆርባዬ የነሱልኛል እያልኩ ሰጋሁ፤ ፖሊሶችም ቢሆኑ ያባትዋ ትእዛዝ አስበርግጓቸው ያን ጨለማ ሲያላቸውን እንዳያሳዩኝ ፈራሁ፤ የውቢቱ በሕግ ትዳኛለህ ማለትም የሕጉ አሠራር አልገባህ ብሎኝ ከረምሁ፤ በኔና ባባትዋም መሐል ሕግ ሲያቆራረኝን እንደማይችል ሳሰላስል ሰነበትሁ።

ይሁን አልኩ፤ ይሁን እንዳሻው ባቦ አልኩኝ፤ ደፈርኩ፤ ማመንታቴን በተንሁት፤ ፍርሐቴን በውሀ አለቅልቄ ከበቀና ወንዝ ውስጥ ጨምሬ በሌት ሰው ለመምታት ለሚያደቡ ጉዴላዎች ተውኩት፤ ሥጋቴን በጨርቅ ቋጥሬ በድቅድቁ ጨለማ ቤት ሠርስረው ለመግባት አንካሴ ለሚተክሉ ወንዶች ሰጧኋቸው፤ የፖሊሶችን ማስደንገጥ እጣቢያቸው ደጅ ድንጋይ ላይ አደረኩላቸው፤ የአባትዋን ከበሬት እኪሳቸው አደረኩላቸው፤ በናትዋ የያዘኝን ይሉኝታ እዚያው በቀሚሳቸው አስታቀፍኳቸው።

ውቢቱ የልብ ልብ አስበቃችኝ፤ የሚርበተበተውን ልቤን በሰቋ አሠረችኝ፤ ፈሪውን ልቤን አጐበዘልኝ፤ የሚንቦጫቦጭ አንጀቴን በተግሳጽዋ አረጋችልኝ፤ በቁጣዋ አበረታችኝ፤ በተግሳፅዋ አጐበዘችኝ፤ በምክርዋ አግባባችኝ፤ በል እንዳለችኝ አልኩት፤ ከቤቴ አገባኋት፤ አገባኋት።

ያ ሁሉ ጭንቅ ያ ሁሉ ፍርሃት፤ ያ ሁሉ መርበድበድ ያ ሁሉ ውቢቱን መሆን ውቢቱን ያለ ወላጆችዋ ፈቃድ ለመግባት ነበር፤ እርግጥ ነገሩ ያን

ሁሉ ያስደርጋል ድረ ገብ ሆና ያልጐለመተችውን የሰው ልጃገረድ ከወላጆችዋ ዘንድ ስቦ መውሰድ ቀላል ነገር አልነበረም፤ ካገባኋት በኋላ ቢሆን ቀንዶዎችን ባየሁና በዩኝ ቁጥር እበረግግ ነበር ፖሊሶች ሲያወሩ ነገር ያለበት ሰው ሲበረግግ ይይዛል ሲሉ እሰማ ነበርና እየተበራታሁ ጨዋ እመስላቸው ነበር፤ ያን ሰሞንም ትዝ ሰሞንም ትዝ የሚለኝ ግጥም ድሮ በልጅነቴ ሴተኛ አዳሪዎች ክራራቸውን በጐናቸው ሸጉጠው እያሳበዱት፤ «ካፒቴን ለገንዘብ ቦርጌስ ለጨዋታ ምን ያንቀረፍፈዋል ቀንዶን ወደ ማታ» የማለት መሰንበቻዬን ትዝ ሲለኝ ከረመ፤ ነገር ያለብኝ ሰው በመሆኔ ለወትሮው ልብም የማልላቸው ፖሊሶች ያን ጊዜ በሠፈሬ መዟዟር አብተው ይታዩኝ ነበር።

የውቢቱ ወላጆችም እግዚአብሔር የገነት ሰው ያርጋቸውና «ከሆነ ወዲያ» ብለው ታርቀውኝ ወዳጅ ሆን፤ እኔም ብሆን ዝተው ከሚተው ልበ ገር አዛውንቶች ጋር በመገናኘቴ ደስ ብሎኛል። ከውቢቱ ወላጆች ጋር ቂም በቀል ሳንያያዝ ካንጀት ተራቀርቀናል። ለመታረቃችን ምሥክር የሚሆነኝም ለዚያን ጊዜው ፋሲካ አንድ ወደል ሙክት ካንድ ኩንታል የነጭ ጤፍ ዱቄት ጋር የስቅለት ለታ ልከውልን የማዕዶት ለታ ደግሞ አንድ ታናሽ፤ አንድ ሸንጥና አንድ ቤተሳልገኝ ልከውልናል። ይህ እኔ ማድረግ የሚገባኝን የተደረገልኝ እኔና ውቢት በተጋባን በሁለት ወር ከአሥር ቀናችን ላይ ነበር።

በኋላም ከውቢቱ ጋር በወግ በማዕረጉ ተፈራርመን የጋብቻውን ወግ አድርሰነዋል፤ ውቢቱም ከገንዘብ ሚኒስቴር ወጥታ ከሌላ መሥሪያ ቤት ሥራ ያዘች፤ የገንዘብ ሚኒስቴሩ ደሞዝ ረብ የለውም ተባለ።

//=//

ይህ ጐደሎ የጦም ቀን ረቡዕ አይሆነኝም፤ ከብቅ ጥልቆቹ ጦሞች ዓርብ ጥቂት ሲሻለኝ ሮብ ግን ፈጽሞ አይሆነኝም፤ ለየጥቃቅኑ በሽታ ሁሉ መታመምንና መቆላበስን ስለምወድ ጉንፋን ያዘኝና መኳንንት ይመስል ለጉንፋን ከቤቴ ተኝቼ ዋልኩ፤ ደግሞም የፋሲካ ሰሞን በመሆኑ የበላሁት ቅባት ሁሉ አልስማማህ ብሎኝ ነበር።

ረቡዕ በመኳንንት ወግ ተኝቼ አረፈድሁ፤ ውቢቱ ወደ ሥራዋ በመሔድዋ ቤቱ ጭር ብሎ ቤት አልመለስ ስላለኝ ሸከላ ላዘፍን ሬዲዮን

ከፊት ሳደርግ ከማዘፊኛው ላይ አንድ የተጣጠፈ ወረቀት አየሁ፤ ሸከላዎቹን ደራቤ ከማዘፊኛው ከከተትኩ በኋላ ፓትቡን «አይአም ኢን ላቭ አጌይን» የሚለውን ዘፈኑን ሲዘፍን ወረቀቱን ማንበብ ጀመርሁ።

«……በከሳሹ ባቶ ለገሰና በተከሳሹ ባቶ ሰለሞን መሐል ስላለው ክርክር ለምስክርነት ስለምንፈልግዎት ሚያዝያ ፳፫ ቀን ከጠዋቱ በ፫ ሰዓት እፍርድ ቤቱ እንድቀርቡ……..» የሚል ለውብቱ የተጻፈላት መጥሪያ ሆኖ አገኘሁት።

ውቢቱ እንደ መጣች በ፯ ሰዓት ተኩል ላይ ስለ መጥሪያው ብጠይቃት «ሰዎቹ የኛ ሠራተኞች ናቸው፤ አንድ ቀን በመሥሪያ ቤቱ እስጥ ተደአብድበው ስለ ነእብረ ለነሱ ምስክርነት ነው» አለችኝ። በነገሩ አዘንኩ፤ ሚስቴም በየአደባባዩ በመጠራትዋ ተበሳጨሁ፤ ሆኖም የመንግሥቴን ሕግ ለማክበር ብቻ ሳይሆን የሚከተላትን መዘዝ ስለማውቅ በቀጠሮ ቀን እንድትሄድ ፈቀድኩላት።

የዕለቱ ዕለት በጠዋት ተነሥተን አብረውን ወደ ፍርድ ቤት ልንሔድ ስንል «አንተ ተመለስ» አለችኝ፤ «ለምን? » ብላት «ምን ትፈጥራለህ? እኔ የምሔደው ለምስክርነት ነው፤ አንተም ወደ ሥራህ ሒድ» ብትለኝ ሚስቴን ብቻዋን ወደ ፍርድ ቤት አልሰዳትም ብዬ አብሬአት ልሒድ ቀረጥሁ፤ እንዲያውም ሴት በመሆንዋ ችሎቱ ያስደነግጣታል፤ ደግሞ ቅሪት ነኝ ብላኝ ነበርና ለልጅ ሰለምጓጓ ብትደነግጥ ዓይናማው ትንቡሼው ያንድ ወር ልጅ ያስወርዳታል በማለት እስዋ ሳትወድ ተከትያት ሔድሁ።

ከችሎቱ ደርሰን የኛዎቹ ሰዎች ተራ እስኪደርስ ካንዳንድ ስዎች ጋር ሆእነን በሽምግልና የያዝናቸው፤ ለገሰና ሰሎሞን ግን እየተጋጋሉ ሔዱ እንጂ የእርቁ መንገድ የማይሆን ሆነ፤ በኋላም የችሎቱ ጠሪ ጠራቸውና ከሳሽ ተከሳሽ ገቡ፤ ጥቂት ቆይቶ ውቢቱ መስካሪዎች ከሚቆሙበት ሳጥን ውስጥ ቆማ ቀኝ እጅዋን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አድርጋ በውነት ልትመሠክር ማለች።

የመሐሉ ዳኛ በሐኪም ምርመራ ባልገዙት መነጥራቸው አናት ዓይናቸውን ሸንጉረው ውቢቱን እያዩ «እነዚህን ሰዎች ታውቂያቸዋለሽ? » ቢሏት እኔ አልደንግጥላትና ውቤት በውስጡ የቆመችበትን ሣጥን በእጅዋ እያሻሸች አቀርቅራ «አዎ» አለች፤ ዳኛው ከተሸጐረች ዓይናእው አንዲቱን

ከድነው ባንዲቱ እያዩዋት፤ «የትኞቹን ነው? እግርሽ ሥር ነው እንዴ ያሉት? » ቢሏት የቀኙ ዳኛ የኮታቸውን ቁልፍ እየቆለፉ ከንፈራቸውን ወደ ታች ስበው «ልጅ አይደለች» አሉ፤ ቀችኑ ረጅሙ ሽማግሌው የግራው ዳኛ «አየሽ እቱ፤ በመጀመሪያ ሰዎቹ የትኞቹ እንደሆኑ እያቸውና ታውቂያቸው እንደሁ ተናገሪ» ቢሉ የመሐሉ ዳኛ ወደ ግራቸው ዞር አሉና «ማወቅማ ሁለቱንም ታቅ የለም፤ ዕውቀቱ ቆይቷል» አሉና «መዘዘ» አሏት።

የቀኙ ዳኛ ከፊታቸው ያለውን ጠረጴዛ ደገፍ ብለው «የተከሰሱበትን ነገር ታውቂያለሽ? » ቢሏት የመሐሉ ዳኛ ወንበራቸውን ተደግፈው ለጠጥ አሉና እየሳቁ «መች አጣችው» ሲሉ በዚያ ያለው ጠበቃና አድማጭ ሁሉ ሳቀ፤ እኔ ግን ሚስቴ ውቢቱ መቀለጃ በመሆንዋ ነደደኝ።

ሳቁ ሲያባራ እኛው የቀኙ ዳኛ «ታዲያስ እቱ» አሏት፤ እስዋም ስትመልስ «አላውቀውም» አለች፤ የመሐሉ ዳኛ ለጠጥ እንዳሉ እግራቸውን በጠረጴዛው ሥር ደራርበው ዘረጉና ወደ ውቤቱ እያዩ «ይነበብልሽ? » ቢሏት ውቢት እንዳቀርቀረች «እኔ ምናውቃለሁ» አለች።

ሽበቶው ራሰ በራ የመሐሉ ዳኛ መነጥራቸውን አውልቀው አስቀምጠውት ስለ ነበረ ከተለጠጡበት ተመልሰው መነጥራቸውን አደረጉና ዶሴውን አስጠግተው የክሱን ምክንያት አነበቡት።

ዳኛው ወረቀቶቹን አንድ ነበሩ መለሱና በንቀት አስተያየት ወደ ውቢቱ እያዩ «ታዲያ? አንቺ አይደለሽ? » ቡሏት ውቢቱ አቀርቅራ ፊትዋ ላይ ላብዋ ችፍ እንዳለበት «አይደለሁም» አለቻቸው፤ የቀኙ ዳኛ «እቱ አትፍሪ፤ ተናገሪ ደሞም ምለሻልና አትዋሺ፤ አለዛ መሐላው ከዚሁ ከፊታችን ያዋርድሻል» ቢሏት ውቢቱ እንዳቀርቀረች ዓይንዋን ወደ ግንባርዋ ሽጉራ በድንጋጤ ተመለከተችና «ምኑ? » አለቻቸው።

«ማላው»

«ታዲያ መቼ ዋሸሁ»

«ማስጠንቀቃችን ነው»

«የተጣላሁት ባንቺ ነው አይደለም»

«ነው»

«ሁለቱንም ባንድ ቀን ነው በየተራ? »

«በሌላ ቀን ነው»

«ምኑ»

«ስለምን ከሥራ ላይ ይዞኝ ሔደ»

«ወዴት»

«ገፈርሳ»

«ለምን? »

«ልንጫወት»

«የመንግሥቱን ሥራ እየተዋችሁ? »

«ታዲያ እሱ አለቃየ ነው»

«እሺ በኋላስ»

«ልክ በ፯ ሰዓት እቤቱ አደረሰኝ፤ በ፱ ሰዓት ሥራ እንደ ገባሁ ደግሞ አብረን ሔድንና በ፲፪ ሰዓት ተሩብ ከቤቴ መለሰኝ።»

«አንቺ ልትሽረሙጪ ነው ሥራ የገባሽው? »

«አይደለም»

«ታዲያስ»

«ደሞዝ እናስጨምርልሻለን ያለዚያ እናስወጣሻለን እያሉኝ ነው»

«ተጨመረልሽ? »

«አዎ»

«ማንኛው ጨመረልሽ? »

«ሰለሞን ነው»

«ለገሰስ? »

«ለገሰ ደግሞ ሁልጊዜ እቢሮዬ እየመጣ ያሳስቀኛል፤ ያቃልደኛል፤ በኋላም የዚሁኑ ነገር ቢያነሳብኝ ነውር ነው አልኩት፤ አንድ ቀን ከቢሮዬ ገባና በሩን ዘግቶ ጡቴን ጭምድድር አድርጎ ይዞ በኃይል ሳመኝ፤ ብቆጣው ጊዜ እንደ ገና ደገመና እንቅ አድርጎ ሳመኝ ከዚያ ቀን በኋላ ተዋደድን»

«ሌላ ቦታ አልተገናኛችሁም? »

«ከማ»

«ከለገሰ»

«ፈለቀች ምሳ ጋብዛኛለች ብዬ ከቤቴ የቀረሁ ለታ እሱ ቤት ነበር የሔድኩት»

«በጄ»

«ይሔው ነው»

«ታዲያ ለምን ተደባደቡ? »

«እንግዲህ እኔ ሰለሞንን አልወደውም፤ አለቃዬ ስለሆነ ነው እንጂ አልወደውም»

«ለምን? »

«በሱ ክፍል ካለነው አንድ ተሾመ ብቻ ወንድ ሲገኝበት የተቀረው በሙሉ ሴቶች ነን፤ ታዲያ ሁላችንንም ተራ በተራ ከቢሮው እየጠራን አጫውቱኝ ይለናል፤ አንዳንዴም ከጭኑ ላይ ያስቀምጠንና ሳሙኝ ይለናል፤ ሰው እንዳይታዘበው ወይም እና እንዳናውቅበት ብሎ ይመስለኛል ወደ ቢሮው ሲጠራን የየግል ሥራችንን አምጡልኝ እያለ ነው። ግን ገብተን ሥርተን ስለማንመለስ ሁላችንም የምንጠራበትን እናውቀዋለን»

«አትቀናኑም»

«አንቀናናም»

«ለምን»

«እኛ የምናየው ደሞዛችንን ነው፤ እሱን ግን እንደ አሻንጉሊታችን አድርገነዋል» ስትል ሰለሞን ከተቀመጠበት ብድግ አለና «ጌታዬ ትሰድበኛለሽና ትታገትልኝ» አለ፤ የመሐሉ ዳኛ ቅልድ ይወዳሉና «አሁን አልሰደበችህ አንተ አሻንጉሊት የሆንካቸው ያን ስለ ነበር ያኔ መጫወቻችን ነበር ነው የምትልህ» አሉትና አወደ ውቢቱ ዞር ብለው «እቱ በይ ቀጥይ» አሏት፤ ውቢቱ ደግሞ «ምን» አለቻቸው።

«ከዚያ በኋላስ»

«ከምኑ በኋላ»

«አለቃችን አሻንጉሊት ነበር አይደል ያልሺው? »

«አዎ»

«በኋላስ»

«ከምኑ በኋላ»

«ካሻንጉሊቱ»

«እሱማ አሻንጉሊት ነበር ብያለሁ»

«እስኪደባደቡ አሻንጉሊት ነበራ? »

«አዎ»

«አይ ለገሰ እግዜር ይይልህ፤ አሁን የልጆች መጫወቻ ባታበላሽ ምን ቸገረህ? » አሉትና ሰውን ሁሉ አሳሳቁት። የቀኙ ዳኛ ከሳቸው ሲያባሩ ወደ ውቢቱ ዞር አሉና «ሰማሽ ማሚቱ፤ ታዲያ እንዴት ተደባደቡ? » ቢሏት «በቦክስና በጥፊ ነዋ» አለቻቸው፤

«አይደለም፤ አየሽ ውቢቱ፤ ነገር እንዴት ተነሣ ነው የምንልሽ»

«ሰለሞን በጥፊ አለው፤»

«ቆይ እንደሱም አይደለም»

«ከዚህ በፊት ተሾመንም መቶታል»

«ማ»

«ሰለሞን»

«ስለምን»

«በናንተው? »

«አዎ በኤልሣ ነው፤ ተሾመ ታዲያ ፈርቶ ዝም አለ፤ እኛም ናቅነው፤ ከያም ወዲህ ከኛ ጋር ተጫውቶም አያቅ፤ ለምን አልመታኸውም? ብንለው ለደሞዜ ነው አለ»

«ሁላችንም ለደሞዛችሁ አወቃችሁበታላ?

«አዎ»

«እሱ ይቆይና የሰለሞንና የለገሰ ጠብ እንዴት ተጀመረ? »

«ተው እቢሮዬ አትምጣ እያልኩ ሁልጊዜ እነግረው ነበር»

«ለማን»

«ለለገሰ»

«ለምን? »

«ጋሽ ሰለሞን ይቆጣል»

«እሱስ ምን ይሻላል? »

«ማ»

«ለገሰ»

«ለገሰማ ባልሽ አይደለ ምናባቱ ቆርጦት ይከለክለኛል ይለኛል»

«ታዲያስ? »

«ታዲያ ያን ቀን ቀን መጣና ስንጫወት ሰለሞን መጣና ምን ታደርጋለህ? ቢለው ለገሰ ሰለሞንን ምን አገባህ አለው፤ አንዳንድ ሲሉ ተደባደቡ»

«መጀመሪያ የተማታው ማነው»

«ሰለሞን ነው»

«በምን? »

«በቦክስ»

«ማን አሸነፈ? »

«እንዴ ሰለሞን እኮ ጋንግ ነው» አሁንም የመሐሉ ዳኛ ትኩር ብለው እያዩዋት «ለመሆኑ አንቺ በሥሪያ ቤት ማደባደብ ወግ ነው? » ቢሏት «እኔ ተደባደቡ አልኳቸው እንዴ» አለቻቸው፤ አሁንም የመሐሉ ዳኛ እንደ ነበሩ ሆነው አተኩረው እያዩዋት በኃዘኔታ «እቤትሽ አቅቀጥሪያቸውም ነበር? » ቢሏት

«እንዴ ጋሽ ጌታቸውሳ»አለቻቸው።

የመሐሉ ዳኛ አውልቀውት የነበረውን መነጥራቸውን መልሰው አደረጉና በብዕራቸው ጠረጴዛውን እየቆረቆሩ «ምንሽ ነው? » ቢሏት «ማ» ብላ ጠየቀቻቸው።

ዳኛውም አይኖቻቸውን ጥብብ አድርገው በትዝብት እያዩዋት «ጌታቸው» ቢሏት ውቢቱ ለጥቂት ጊዜ ተከዛ ስታመነታ ቆየችና እንዳቀረቀረች በእረፍት አነጋገር ቃሏን አለስልሳ ቀስ ብላ «ባሌ ነዋ» አለቻቸው።

«ዓውድ ይጣልሽ» አሏት የመሐሉ ዳኛ፤ ወዲያውኑ «ለመሆኑ ይህን ጉድ ያውቅቃል? » ቢሏት «መቼ? » አለቻቸው፤ ዳኛው መነጥራቸውን አውልቀው ጠረጴዛው ላይ ወረወሩና ወደ ኋላቸው ደገፍ ብለው «ድሮስ ሆነ አሁን? » ቢሏት ውቢቱ እንዳቀረቀረች ሰርቃ አይታው «አያቅ ይሆናል» አለቻቸው።

የቀኙ ዳኛ በቀኝ እጃቸው ጉንጫቸውን ደግፈው ጠረጴዛው ላይ እንደተመረኮዙ አዝነው «ለመሆኑ አሁን የት ነው ያለው? » ቢሏት ውቢቱ ቀና ብላ አይታቸው «አለ» አለቻቸው፤ የግራው ዳኛ የአፍንጫቸውን ቆዳ አጨማደው በክፉ አሰተያየት ሲያዩዋት የመሐሉ ዳኛ ደግሞ በእግራቸው መሬቱን እየቆረቆሩ ሲተክዙ የቀኙ ዳኛ እንዳዘኑ «የት ነው? » ቢሏት ከነበርኩበት መቀመጫዬ ከሕዝቡ መሐል ተነስቼ ከረባቴን አስተካከልኩና በዚያ ሁሉ ባፈጠጠብኝ ዓይንና ምን ሊናገር ተነሳ ብሎ አፍ አፌን በሚጠባበቀው በችሎቱ ሕዝብ መሀል «እዚህ ነኝ» ብዬ ተዋወኳቸው።

# ምዕራፍ ፯።

መፈጠሬን ጠላሁ፤ ወንድ ልጅ ተወለደልን ብለው የምሥራች የነገሩበትን ቀን ረገምሁ፤ ከተማ ተወልጄ እንዳድግ ያደረገኝን አምላክ አማሁት፤ ደበሎ ለብሰው አሹቅ እየገተሙ በጎች እየጠበቁ በባላገር አድገው በዚያ ተጋብተው ከኖሩት ሰዎች እንደ አንዱ ያላደረገኝን እግዜርን አማረርኩት።

ተማሪ ቤት ግባ ብለው እናቴ የተናገሩበትን አፋቸውን ጠላሁት፤ ደብተር የገዙልኝን ዘመዶቼን አሽጓጠጥኳቸው፤ ፊደል ቁጠር ብለው እጄን የመሩኝን መምህር ረገምኳቸው፤ ካጭበርባሪዎች ጋር አጭበርባሪ በመሆኔ መፈጠሬ ስለቸኝ፤ መወለዴም አንገፈገፈኝ፤ መረረኝ፤ ትዳር የሚባል ቃል ስሰማ እንባዬ ያቀር ጀመር፤ የትዳር ሱስ ጸናብኝ የፍቅርን አቦል እንጂ እስከረጃው የሚዘልቁ በማጣቴ በፍጡሮች አዘንኩባቸው፤ ፈጽሜ ላላገባ ቆረጥሁ፤ ግና ሕሊናዬ በትዳር ፍቅር ተመርዞ ጸጥታ ነሳች፤ መበሳጨት

በዛብኝ፤ ኑሮዬ ቀፈፈኝ፤ ገረዶች እያሽኮረመሙኝ መኖሩም ሲኦል መሰለኝ። የገረዶቼ ግብዣም ሱሪ መታጠቄን አስጠላኝ።

አቶ በላቸውም መልካም መካሪዬ ሆነኝ፤ እኔም እሱም እማማ የምንላቸውን እማማ በላይነሽን እንዳገባቸው መከረኝ፤ ጠላኋቸው፤ ናቅኋቸው፤ እማማ በላይነሽ ቤቴን አከራይቼ የተከራየሁት ቤት ባለቤት ናቸው፤ ባላቸውን ቀኛዝማች ካብትህ ይመርን ከሬቱ ሦስት ዓመት ሆኗቸዋል። እማማ በላይነሽ ብዙ ሀብት እንደ አላቸው አውቃለሁ።

አንድ አሽከር ላንድ ጌታ በበቃበት እመን እማማ በላይነሽ ከዘበኛው ሌላ አራት ጠርንገሎ አሽከሮች አሏቸው፤ እማማ በላይነሽ ረዘም ወፈር ያሉ ጠይም አሳ መሣይ ናቸው፤ እማማ በላይነሽ አዘውትረው የአበሻ ቀሚስ ስለሚለብሱ ደበክበክ ያሉ ወይዘሮ ናቸው፤ የእማማ በላይነሽ ዓይኖች ትልልቆች በመሆናቸው በጥርሳቸው ስቀው በዓይናቸው ሲቃኙ ደስ ይላሉ።

ከእማማ በላይነሽ ጋር መቃለድ ጀመርኩ፤ እየተጠራሁ ራት ለመብላትም በቃሁ፤ ውስኪም አጋበዝ ጀመር፤ አልረሳውም ሦስት እንቁላልና ሁለት መላላጫ የበለሁበት ማታ ከሳሎን ቁጭ ብለን ውስኪ እንጠጣ ጀመርን።

እማማ በላይነሽ እያሳሳቁኝ ሦስት ብርጭቆ ውስኪ ጠጣሁ፤ እግሬ እግራቸውን ነካ ባደርጋቸው አንገቴን ሳብ አድርገው እጉያቸው ጨመሩኝና በኩርኩም ገጨት አደረጉኝ፤ ደስ አለኝ፤ የሴት የቀለዶ አመታት እንደሚያደርገው ሁሉ የደስታ ትኩሣት ተሰማኝ፤ አላበኝ ልቤ ድው ድው ይል ጀመር።

ከእማማ በላይነህ ጋር ጨዋታ ጀመርን፤ «እማማ በላይነሽ ደግ ኖት እኮ» ብላቸው «አዎ» አሉኝ

«ቆንጆ ኖትኮ»

«አውቃለሁ»

«ግዙፍ ሁኑ እንጂ ልጅ ኖትኮ»

«መች አጣሁት»

«ለምን ባሎን ፈቱ? »

«ጠላኛ»

«እርስዎን? »

«አዎ»

«ለምን»

«እንጃባቱ»

«አሁን ለምን አያገቡም? »

«ታመጣልኛለህ? »

«መቼስ ስሜት ነው»

«ምኑ? »

«ልክ ነው፤ ሁሉም ነገር በስሜት ነው»

«የምኑ»

«የውስኪው»

«ሱሰኛ ነህ? »

«ኖ የስሜት ነው»

«የውስኪ ስሜት? »

«የሰው ቢሆን ይሆናል»

«እንዴት ያለ ሰው»

«ለምሳሌ እኔ እማዬን እወዳቸዋለሁ»

«እናትህን? »

«እህቶቼንም»

«የተወለዱህን? »

«ባይወለዱም ስሜት ነው»

«እንዴት ነው ስሜት»

«ለምሳሌ ጊደሪቱን በሬው ያጠቃታል»

«ታዲያስ? »

«ወጠጤውን ደግሞ እናቲቱን ፍየል»

«የቱ ፍየል? »

«ያቶ ዱባለ»

«የቱ ዱባለ? »

«አዎ የጋሽ ዱባለም ቢሆኑ ትልቅ ናቸው»

«ምናቸው? »

«ሴተዮዋቸው»

«የቷ ሴትዮ? »

«ስልሳ ዓመት ይሆናል»

«የምኑ? »

«የስሜት ነው»

«ሰከርክ? »

«ምነው እማማ በላይ እርሶዎ ጋብዘው»

«ታዲያ ስሜት ስሜት ብቻ ትላለህ»

«ይሄ ትቤቶ ስንት ክፍል ነው»

«ስምንት»

«ይሔ በር ወዴት መሔጃ ነው? »

«ወደ መጻሕፍት ቤት»

«ቀጥሎስ? »

«ወንዳንደኛው ሳሎን»

«ቀጥሎስ? »

«ወደ መልበሻ ቤት»

«ማጌጥ አልፈልግም በዚህስ? »

«ወደ መኝታ ቤት»

«እማማ በላይነሽ አሁን ብሰክርስ? »

«አስተኛሃለሁ»

«አሽከሮቾ እየሳቁብኝ? »

«ማንም ሳያይ»

«እንዴት አድርገው? »

«ሰክረህ እየኝ»

«ጥዋት ብንን ብል ደነገጥሁ፤ ባስታውስ አስታወስሁ፤ በዚያ ሰፊ አልጋ ላይ ቀኝ ክንዴ ላይ ዘፍ ወዳለው ሞንዳላ አንገት ላይ ከበላይነሽ ጋር ዓይን ለዓይን ግጥም አልን፤ «ሳትሞኝ ጸድቀሻል» ብል «አንቺ ሆንኩ? » አለችኝ።

//=//

ፊታውራሪ አውግቸው፤ አቶ ይልማ፤ ግራዝማች ገብሬ ባሉበት ተፈራርመን ከበላይነሽ ጋር ተጋባን። ከዚያው ቤት ልወጣ ያንድ ወር ረፍት እንዳደርግ ማዘዣ ደረሰኝ፤ በትእዛዝ ያንድ ወር ረፍቴን ተሞሽርኩበት፤

አማርረው የነእብርኩትን አምላክ እንደ ገና ክብርህ ይስፋ እያልኩ እመርቀው ጀመር።

እየቆየሁ የታሠርሁ መሰለኝ፤ ከምድረ ግቢውም እንዳልወጣ ተከለከልኩ፤ ለጦርነት ቀን እንዲዋጋ ታፍኖ እንደሚቀለብ ፈረስ ሥራዬ መቀለብና መተኛት ሆነ። እንኳን ሴቶች ወንዶች ካጠገቤ እንዳይደርሱ አደረገች፤ ስሳሳትም በጥፊ ትለኝ ጀመር። ልፊያዋም ስለቸኝ፤ ከሷ ጋር የምናደርገው ጨዋታ መላ ቅጥ ስላጣ አንገሸገሸኝ።

ከምድረ ግቢይቱ የመውጫ ቀኔ በየሳምንቱ ቅዳሜ አምቦ ወይም በሸፍቱ በመኪናዋ ወርደን የምናደርገው ብቻ ነው፤ ሻንቅላ የነበረ ቆዳዬ ፈጐ ቀይ ዳማ ሆንኩ፤ ግን ፍጹም ነፃነት የለኝም ነበር፤

በውጪ እንደፈለጋቸው የሚራወጡት ወንዶች አስቀኑ፤ የድሮው ኑሮዬ ብናፍቀው የማይገኝ ሆነ፤ ያሁኑ የምግብ ዓይነት ጎተራነቴን በድሮው ረሃቤ፤ ልለውጥህ በልው አልገኝ አለ፤ ያቺ ባንድ መጠነኛ ክፍል የተወሰነችው አልጋዬ ናፈቀችኝ፤ እኔ አለሁ፤ የምናፍቀው ግን የለም።

ልለቀቅ ስል ከበላይነሽ የሚደርስብኝ ቁጣና ዛቻ ያስደነግጠኝ ጀመር፤ አዘውትራም ካልፈታሁህ ልትፍታኝ አትችልም ትለኝ ጀመር፤ በላይነሽን ስመኢት እንው እያለች የለፈለፈችላትን ምላሴን እነክሳት ጀመር፤ እንዳልቆጣትም እንዳልንተአብተብ ሰጋሁ፤ መብሌ ሁሉ ሬት ሆነብኝ።


ፍጹም ለማዳ ሆንኩ፤ ሁሉን ነገር ረሳሁ፤ በላይነሽን እንደ አምላኬ ተንበረከኩላት በሀባቷም ገብቼ መቆጣጠር ጀመርሁ፤ ስታጠፋም እገስፃት ጀመር፤ አምቦ ያለውን ቤቷን እየወረድን አሠርተን እንደ ጨረስን የቢሾፍቱውን ተመላልሼ አሠራሁላት፤ እንደ ወንድነቴ ልፈታሽ እምብት አለኝ ማለቴን ረስቼ በተኛን ቁጥር እንድንቆርብ እጠይቃት ጀመር፤

በላይነሽን ደስ ይላት ጀመር፤ ለበላይነሽ እውነተኛ ባሏ እንደሆንኩላት እሷም ሆነችኝ፤ ግና የእኩልነቱ ቀርቶ ባሎች ለሚስቶች የሚሰጧቸውን መብት ሩቧን ያህል እንኳ ተነፈግሁ።

ልክ ከበላይነሽ ቤት ገብሬ ከሥራዬ በወጣሁ በምንተኛው ወሬ በላይነሽ አምቦ እርዳ እስከትመጣ አንድ ደብዳቤ ጻፍኩ፤ «ዛሬ ፈታሁሽ፤ ደህና ሁኝ፤ ምንም ሳልነካብሽ በነፃ እንደ ገባሁ በነፃ ወጣሁ፤ ተገላገልኩሽ»

እነዚህ ቃላት ያሉበትን ወረቀት አጣጥፌ ዘወትር ስትገባና ስትወጣ ከመታየው መስተዋት ላይ አጣብቄላት ሾከክ አልኩ።

ደብረ ብርሃን ሔጄ ከአክስቴ ከወይዘሮ ንጋቷ ዘንድ በተቀመጥሁ በ፲፫ኛው ቀን በዘበኛ ተይዤ አዲስ አበባ ገባሁ፤ አዲስ ኧብባ በገባሁ በስምንተኛው ቀን በማላውቀው ነገር ተፈርዶብኝ አቃቂ ወህኒ ቤት ተላክሁ፤ ከሚደላኝ ወህኒ ቤት ወጥቼ ከማይደላኝ ወህኒ ገባሁ።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታችው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸ። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)
5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)

9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY